ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የተማሪዎች የአረዳ ቃላት አጠቃቀም በቋንቋ ክሂሎች ላይ ያለው ተጽእኖ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች

በ

ብርሃኑ ገብረአብ

የኤም.ኤ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር ሥነ-ዘዴ ለማሟላት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች መካከል ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

ጅማ

ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የተማሪዎች የአረዳ ቃላት አጠቃቀም በቋንቋ ክሂሎች ላይ ያለው ተጽእኖ በአዲስ አበባ ከተማ በተማሪጡ ሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች

በ

ብርሃኑ ገብረአብ

የኤም.ኤ ዲግሪ አማርኛን በማስተማር ሥነ-ዘዴ ለማሟላት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች መካከል ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2009 ዓ.ም
ጅማ

ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የተማሪዎች የአረዳ ቃላት አጠቃቀም በቋንቋ ክሂሎች ላይ ያለው ተጽእኖ በአዲስ አበባ ከተማ በተሚጠሁለተኛ እና መሰናዶ ትምህርትቤቶች

**የፈተና ቦርድ አባላት**

የዋና አማካሪ ስም ፊርማ

_______________________ ________

________

የረዳት አማካሪ ስም ፊርማ

_______________________ _______________

የውጭፈታኝ ስም ፊርማ

_______________________ ________

________

የውስጥ ፈታኝ ስም ፊርማ

_______________________ ________

________

# ምስጋና

ይህን ጥናት ጀምሬ እስክጨርስ በቅርብ ሆነው በማብረታታት እና ጥናቱ አጥጋቢ ሆኖ ሊዘጋጅ የሚችልበትን ማንገድ በማሳየት ውድ ጊዜያቸውን ለሰውልኝ ለማማስገን የማቀደሙው ለዶ/ር አቢይ አሰፋ እና ለረዳት አማካሪዬ ረዳት ፕሮፌሰር ጥበቡ ሽቴ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡በመቀጠል የዚህን ጥናት ወጪ ለሸፈነልኝ ጅማ ዩኒቨርሲት ወሮታው ምንጊዜም አይረሳምና ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሰው፡፡

እንዲሁም ይህንን ጥናት በምሰራብት ጊዜ ለተባበሩኝ የትምህርት ቤቶች አስተዳደር እና በዚህ ጥናት ላይ ለተሳተፋችሁ ውድ ተሳታፊዎች ያለናንተ ተሳትፎ እና ቀና ትብብር የዚህ ጥናት አላማው አይሳካም ነበር በመሆኑም የከበረ ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በትየባውም ላይ ሳትሰለች ለተባበርሽኝ ወ/ሪት መሰረት አይችሉህም ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻም ከውድ ጊዜያችሁ ላይ ቀንሳችሁ መረጃ በማሰባሰብ፣ጥናቱን በማንበብ የበኩላችሁን ገንቢ አስተያየት እና እርማት ላደረጋችሁልኝ ውድ ወዳጆቼ መምህር አደም ሀሰን፣እሸቱ አያኖ፣ብርሃኑ ተረፈ፣አሰለፈች አዱስ አና አቦነሽ ማግስቱ የከበረ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

**ማውጫ**

**ይዘት**

**ገፅ**

**ምስጋና** ........................................ i

**ማውጫ** ........................................ ii

**ሠንጠረዥ ማውጫ** ........................................ iv

**አጠቃሎ** ........................................ vi

**ምዕራፍ አንድ** ........................................ 1

**መግቢያ** ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 3

1.3 የጥናትና ምርምሩ ዓላማዎች ........................................ 4

1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ ........................................ 4

1.3.2ዝርዝር ዓላማዎች ........................................ 4

1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄ ........................................ 4

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ 4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................ 5

1.7 የጥናቱ ተግዳሮቶች ........................................ 5

1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ ........................................ 5

**ምዕራፍ ሁለት** ........................................ 6

**የተዛመጅ ጽሁፍ ቅኝት** ........................................ 6

2.1 የአራዳ ቃላት ምንነት ........................................ 7

2.2 የሚደበኛ ቃል ስያሜ ........ 8
2.3. የኢ- ሚደበኛ ቃል ስያሜ ........ 9
2.4 የአራዳ ቃላት በማ ተፈጠሩ? ........ 11
2.5 የአራዳ ቃላት ባህሪያት........ 135
2.6 የውሰት /Borrowing/ ምንነት ........ 157
**ምዕራፍ ሦስት........ 17**
**3.1 የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........ 17**
3.2 የመረጃ ናሙና አወሳሰድ ስልት........ 17
3.2.1 የጥናቱ ቦታ........ 20
3.2.2 የጥናቱ አካላይ ........ 201
3.2.3 የናሙና ብዛት መወሰን ........ 22
3.2.4 አመቺ ወይም ግኝት ናሙና ዘዴ........ 222
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ **Error! Bookmark not defined.**
3.3.1 ምልከታ........ **Error! Bookmark not defined.**
3.3.1.1 በአቻ ተሜዎች መረጃ መሰብሰብ........ **Error! Bookmark not defined.**
3.3.2 ድርሰት ማፍ........ **Error! Bookmark not defined.**4
3.3.3 የጽሁፍ መጠይቅ ........ **Error! Bookmark not defined.**
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ........ 22
**ምዕራፍ አራት........ 237**
4.1. የመረጃ ትንተና ወጤት........ 237
4.1.1 የተሳታፊዎች ዳራ ትንተና ........ 247
4.1.2 ከምልከታ የተገኘው የወጤቱ ትንተና ........ 247

4.1.3 ከተሜዎች ደርሰት ውስጥ የተገኙ የአራዳ ቃላት ትንተና ውጤት..................................... 31

4.1.4 የክፍትና የዝግ መጠይቅ ትንተና........................................................ . 32

4.1.4.1 ከክፍት ጥያቄ የተገኘ ትንተና
……………………………………………………….51

4.2 የግኝት ማጠቃለያ.................................................................................................. 443

**ምዕራፍ አምስት.......................................................................................................... 487**

**የማጠቃለያና መፍትሄ ሃሳቦች............................................................................... 487**

5.1 ማጠቃለያ ............................................................................................................ 487

5.2. መፍትሄ ሀሳብ.................................................................................................... 499

**ዋቢ ጽሁፎች. ................................................................................................................... 60**

**አባሪዎች**

**ሠንጠረዥ ማውጫ**

**ሰንጠረዥ 1፡ የጥናቱ አካላይ ዝርዝር .............................................**Error! Bookmark not defined.**1**

ሰንጠረዥ 2፡ የጥናቱ ናሙና በየትምህርት ቤቱ ዝርዝር........................Error! Bookmark not defined.2

ሰንጠረዥ 3፡ የተሳታፊዎች ዳራ........................................................................... 247

ሰንጠረዥ 4፡ አዲስ ወይምአመጣጣቸው ያልታወቀ ቃላትን በመፍጠር የተገኙ የአረዳ ቃላት.................... 248

ሰንጠረዥ 5፡ ተጨማሪ ትርጉም በመስጠት የተፈጠሩ የአረዳ ቃላት ................................................ 259

ሰንጠረዥ 6፡ በምክላ ትርጉም በመስጠት የተፈጠሩ የአረዳ ቃላት..................................................... 31

ሰንጠረዥ 7፡ ከውጭና ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በውሰት የተፈጠሩ የአረዳ ቃላት............................... 282

ሰንጠረዥ 8፡ ቃላቱ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማለባበጥ የተፈጠሩ የአረዳ ቃላት............................ 293

ሰንጠረዥ 9፡ የአረዳ ቃላት አጠቃቀም.................................................................................. 327

ሰንጠየዥ 10፡ የአረዳ ቃላት ለምን ተግባር ነው የሚውሉት? ........................................................ 349

ሰንጠረዥ 11፡ በትምህርት ቤት ውስጥ የአረዳ ቃላት የሚዘወተሩት ተማሪው በምን ሁኔታ ውስጥ ሲሆን ነው?..................................................................................................................3540

ሰንጠረዥ 12፡ አረዳ ቃላት አጠቃቀም በትምህርት ቤት.............................................................. 36

ሰንጠረዥ 13፡ የተግባቦት ክፍተት......................................................................................... 37

ሰንጠረዥ 14፡ የአረዳ ቃላት እውቀት ጠቀሜታ.......................................................................... 46

ሰንጠረዥ 15፡ የአረዳ ቃላትን ተለዋዋጭነት በተመለከተ.............................................................. 418

ሰንጠረዥ 16፡ የአረዳ ቃላት በየትኛው የቋንቋ ክሂል ላይ ይታያል/ይደመጣል?................................. 50

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም በቋንቋ ክሂሎች ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመመርመር ሲሆን በአካሄዱም አይነታዊ የምርምር ዘዴን መሰረት አድርጓል፡፡ መረጃዎችን ለማንተን ገላጭ ተንታኝ የትንተና ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ይህ ጥናት አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት በሚማሩ 443 ተማሪዎችን አመቺ /ግኝት/ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ በጥናቱ ላይ አሳትፏል፡፡ አጥኚው ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች (1) በትምህርት ቤት ተማሪዎች እየተጠቀሙባቸው ያለው የአራዳ ቃላት አፈጣጠር ምን ይመስላል?፣ (2) የአራዳ ቃላት በየትኞቹ ክሂሎች ላይ ተጽእኖው ይታያል?፣ (3) የአራዳ ቃላት ተለዋዋጭነት በተማሪዎቹ ተግባቦት ላይ የሚፈጥረው ተጽእኖ አለ? (4) የአራዳ ቃላት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የአገልግሎት ስርጭቱ ምን ይመስላል? የሚሉት ሲሆኑ ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ያገለገሉት ምልከታን በመጠቀም የተማሪዎችን ንግግር በማዳመጥ የተናገሯቸውን ቃላት ማዛግቧል፣ በተማሪዎች የተሰበሰቡ የአራዳ ቃላት፣ በተማሪዎች የተጻፉ ደርሰቶችንና በጽሁፍ መጠይቅ የሰበሰባቸውን መረጃዎች ተንትኗል፡፡

በዚህም መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚሳየው ተማሪዎች የአራዳ ቃላትን በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ካሉ ቢጤዎቻቸው ጋር እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ የቃላት አፈጣጠሩም የአማርኛ መደበኛ ቃላትን ገልብጦ በማስበብ፣ አዲስ ቃል በመፍጠር፣ ለመደበኛው የአማርኛ ቃል ተለዋጭ ትርጉም በመስጠት፣ ከሌሎች ቋንቋዎች በመዋስ እንደሚፈጠሩ ጥናቱ ያሳያል፡፡ እነዚህ የአራዳ ቃላት በተወሰኑ ቡድኖች የሚፈጠሩና ተጠቃሚዎቹ ብቻ የሚያውቋቸው ሲሆኑ አገልግሎት የሚሰጡት ሌሎች የህብረተሰብ አባላት እስኪያውቋቸው ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ የቃላቱን ፍቺ ሌሎች ካወቁት ምስጢራዊነታቸው ስለሚበቃ በሌላ ቃል ይተካሉ፡፡ ይህ ደግሞ የቃላቱን ተለዋዋጭነት ያሳያል፡፡ ስለዚህም መምህራን ቃላቱን በትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ከተጠቀሙ በመደበኛ ቃላት ተክተው እንዲጠቀሙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ መግባባት ለግለሰብ እንዲሁም ለማኅበረሰብ የሰው ዘር ልዩ እና በሁሉም ዘንድ ያለ አለመቀፋዊ መሳሪያ ነው፡ የሰው ልጅ አቅም ተምሳሌታዊ እሳቤዎችን ለመተርጎም እና ትርጉም ወዳለው ድምፅ-ልሳን በማውጣት ቋንቋን ፈጥሯል፡፡ የሰው ልጅ ባህል፣ ማህበረሰባዊ ባህሪያቱና አስተሳሰቡ ከቋንቋ ውጪ እውን መሆን አይችልም፡ በሌላ አባባል ደግሞ ተግባቦት ያለሃሳብ ትርጉም አይኖረውም፡ ለተግባቦት ደግሞ መሰረቱ ቃላት ናቸው፡

ቃላት በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ተግባቦት ውስጥ በዋናነት የሚገለገሉ የማናገርና የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ያላቸው የቋንቋ ክፍሎች በመሆናቸው አጥኚው የአራዳ ቃላት በተማሪዎች የማናገርና የመፃፍ ክሂል ውስጥ ያላቸውን የስርጭት መጠን በመመርመር በተግባቦት ክሂል ውስጥ ያለውን ስርጭት ፈትሿል፡፡ ቋንቋን በተመለከተ (Haliday፣1978፣1) ሲገልጽ "የሰው ልጆች በቋንቋ አማካይነት ባህሉን፣ እምነቱን፣ ፍላጎቱንና አመለካከቱን የሚገልጽበት መሳሪያ ነው" ይላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋው ባለቤት የሆነው ማህበረሰቡ ውስጥ የተገኙ ልማዶች፣ በእለት ተዕለት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የአለባበስና የአመጋገብ ባህሉንና ሌሎች ባህሪያቱን ጨምሮ ከሚለዩባቸው አንዱ ቋንቋ ነው፡ የሰው ልጆች ቋንቋን በሚግባቡበት ጊዜ በቃላት አጠቃቀም ልዩነት ምክንያት በንግግር ክሂል ላይ ከመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ወጣ ባለ መልኩ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡ ይህንንም ከሚያደርጉት መካከል በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ ወጣት ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ በምስጢር ለማስተላለፍ የሚጠቀሙት ነው፡

በህበረተሰብ ውስጥ በማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ ከሚውሉ ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም መካከል አንዱ የአራዳ ቋንቋ ነው፡ ቃሉ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ በግልፅ የተከሰተው በ18 ኛው መቶ አጋማሽ ላይ ሲሆን በዚህ ዘመን ወራዳ ባህሪ ያላቸው ቡድኖች የሚጠቀሙትን ቋንቋ ለማመልከት እንደነበር እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ ቃሉ የጎረምሶች ቋንቋ ከሚል ትርጉም ጋር ተያይዞ ይገኛል (አብነት፣2007)፡፡ የአራዳ ቋንቋ በህብረተሰቡ ዘንድ አንዳንድ ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት የዱርዬ፣ የወሮበላ ቋንቋ ነው ይላሉ፡ ሌሎች ደግሞ በወሉ ያልተያዙ አንዳንድ ዋልጌ ወጣቶች የፈጠሩት መግባቢያ ነው ሲሉ የተቀሩት ደግሞ የዘመኑ ከተሜ ቀመስ ወጣቶች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው ሲሉ ይበይኑታል፡፡ (ምትኩ፣1983) ሰለሞን፣(1997)እና አስቴር፣(2000) ይህንን አሳብ ሲያጠናክሩት የአራዳ ቃላት ተጠቃሚዎች በከተማ የሚኖሩ ወጣቶች ናቸው፡ ወጣቶቹ፤ በትምህርት ቤት የሚገኙ ጥቂት ወጣት ወንዶችና ሴት ተማሪዎች ሌቦች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች የታክሲ ረዳቶች ወዘተ. ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡

ይህንን መሰረት በማድረግ አጥኚው በትምህርት ቤት ውስጥ የአራዳ ቃላት አጠቃቀም በተማሪዎች አገልግሎት ላይ ሲውል በማጃመጡእና ደርሰት ሲጽፉም ቃላትን በማገኘቱ ለርዕሰ ጉዳዩ ትኩርት ሊሰጠው ችሏል፡፡

የአራዳ ቃላት የሚባለው ከሌሎች መግባቢያዎች የሚለየው ባለው ታሪክ፣ ባፃፃፉና በትርጉሙ ብቻ አይደለም፡፡ የአራዳ ቃላት ይበልጥ ተስማሚ በሆነ መንገድ የሚለፀው ቃላቱን ማን ይጠቀምበታል?፣ በቃላቱስ ምን ሜልክት ይተላለፋል? ከሚሉት ጥያቄዎች ከምናገኘው ሜልስ ጭምር ነው፡ በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ የዘመን አመጣሽ አባባል የሚታወቀው በሚጠቀሙባቸው ቃላት አይነት እና በሚሰጡት ትርጉም ብቻ ሣይሆን ቃላትና አባባሎቹን የሚጠቀሙባቸው ሰዎች አንፃር ነው (ምትኩ፣ 1983)፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ አጥኚው ተማሪዎች በአራዳ ቃላት የአጠቃቀም ስርጭትን ለመመርመርና ከቋንቋ ትምህርት አላማ አንፃር ያለውን ክፍትት ለማሳከት ጥረት አደርጓል፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረቱን የሚያደርገው የአራዳ ቃላት አጠቃቀም በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በመናገር እና በመፃፍ ክሂል ውስጥ ያለውን የስርጭት መጠን ሜቲተሽ እና የሚያሳድረውን የተግባቦት ክፍተት ከአማርኛ ትምህርት አላማ አንፃር ፍተሻ ማድረግ ነው፡ የአማርኛ ቋንቋ በሀገራችን በብዙ ተናጋሪዎች ዘንድ የሚነገርና የሀገሪቱም የፌደራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኖ በማገልገል አያሌ ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ በመሆኑም አጥኚው በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለተኛ እና የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም በመናገር እና በመፃፍ ክሂል ውስጥ ያለውን የስርጭት መጠን በሚያበኛው የተግባቦት ሂደት ላይ ተጽእኖ መኖሩን እና አለመኖሩን መመርመር ነው፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው በመምህርነት ዘመኑ አልፎ አልፎ ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን በመጠቀም መልዕክት ሲያስተላልፉ ምን ማለት እንደፈለጉ ግር ስላለው ይህ ግርታው በሌሎች ተማሪዎችና መምህራን ዘንድ ይኖር ይሆን? የሚል ጥያቄ ሁሌ ጊዜ በውስጡ ይመላለስበት ነበር፡፡ በመሆኑም ዘመኛ ወጣቶች የሚጠቀሙት ቃላት ማብራከት ከቋንቋ ትምህርት አላማ አንፃር ሲያስበው በውስጡ የተፈጠረው ለቋንቋው እንግዳ መሆን በተማሪዎች ውስጥ ቢኖርስ? የሚል ጥያቄ ስለፈተነው ይህንን ጥያቄ በጥናት ለማረጋገጥ በሚል መነሻ ሀሳብ ጥናቱን አጥንቷል፡፡ አጥኚው በአዲስ አበባ ከተማ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች የአራዳ ቃላትን በንግግር ሂደታቸው እንዴት እና በምን አውድ ውስጥ እንደሚጠቀሙት ለመመርመር በማሰቡ እና ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ በቡድን ሆነው በሚጋገሩበት ጊዜ የሚጠቀሙት ቃላትን እንግዳነት በማንዘብ የቃላቱን ምንነትና ለምን እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ካለው ፍላጎት የተነሳ ቃላቱ ለተማሪዎቹ የሚሰጡት ግልጋሎት እና ምንነትን በመመርመር የቃላቱን ትርጓሜ የማያውቁ ተማሪዎች ጋር ሲደርስ የሚፈጥረው የተግባቦት ክፍተት መኖሩን እና አለመኖሩን አጥኚው በመመርመር እና በተግባቦት ላይ የሚያስከትለውን ክፍተት ማየት ነው፡

በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ በተለያዩ የማከን ደረጃ ቡድናዊ የቋንቋ አጠቃቀሞች አሉ፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ Crystal (1995) ሲገልጽ "የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የግል ጥቅማቸውን ማስፈጸሚያ ሲሉ የሚጠቀሙት ነው፡ ይህ ቋንቋ ከአንድ ማህበረሰብ የቋንቋ አጠቃቀም የተለየና ከቡድን ውጪ የሆኑ አባላት ለረዱትና ለገነዘቡት የማይችሉና ግልጽነት የሌለው የቋንቋ አጠቃቀም ነው፡ ይሁን እንጂ ቋንቋው ለቡድኑ አባላት ግልጽነቱ በጣም የጎላ ነው" በማለት ይገልጻል፡፡

ቡድናዊ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ Pemario (1990፣69) ጥናትና ምርምር በማካሄድ በጥናቱም ማጠቃለያ ላይ የሚከተለውን ሀሳብ ይገልጻል፡፡ "የቡድን ቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ነባር ቃላት ላይ ተጨማሪ ትርጉም በመቀጠልና አዳዲስ ቃላትን በመፍጠር የተገኘ፣ በቃላት አፈጣጠሩ የሥነ-ልሳንን መሰረታዊ ሀሳብ የማይከተል፣ በጠቅላላው የተወሰኑ ማህበራዊ ክፍል ቡድኖችንና የእድሜ እኩዮችን የሚያገለግል የአጠቃቀም ስልት ነው" በማለት ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደረጀ (1996) ስለ ቡድናዊ እና የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ሲገልጽ የቡድናዊ ቃላት ወይም የአራዳ ቃላት የሚባሉት የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ወይም ቡድኖች የቡድናቸውን የውስጥ ምስጢር ለመጠበቅ ወይም ጥቃትን ለመከላከል በቡድኑ ውስጥ ብቻ መረጃ ለማለዋወጥ ሲሉ ከመደበኛ የቋንቋ ቃላትና ስርዓታዊ አጠቃቀም በተለየ ሁኔታ የሚፈጥሩት የመግባቢያ ዘዴ ነው በማለት ይገልጻል፡

ይህንንም መሰረት በማድረግ አጥኚው ቡድናዊ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት በሚማሩ ተማሪዎች በቡድን የሚጠቀሙት የአራዳ ቃላት በመናገርና እና በመፃፍ ክሂል ላይ የሚፈጥረው የተግባቦት ክፍተት መኖሩን ዓይነታዊ

የምርምሮ ዘዴን በመጠቀም በተገቢው ሁኔታ ተንትኗል፡፡በተጨማሪም የአራዳ ቃላት በማገር እና በማፍ ክሂል ላይ ያለውን የአገልግሎት አድማስ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማ አንፃር ፈትሿል፡፡

## 1.3 የጥናትና ምርምሩ ዓላማዎች

### 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

ይህ ጥናት የተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም በቋንቋ ክሂሎች ላይ ያለውን ተጽእኖ ከቋንቋ ትምህርት አላማ አንፃር በመመርመር ቃላቱ በሚደበኛው የተግባቦት ሂደት ላይ የሚፈጥሩትን ክፍተት ማሳየት፡፡

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

1. የአራዳ ቃላት ተለዋዋጩት በተግባቦት ሂደት የሚፈጥረውን ተጽእኖ ማዘርዘር፡፡
2. የአራዳ ቃላት ተማሪዎች በየትኛው ክሂል ውስጥ እየተጠቀሙት እንደሆነ ማሳየት፡፡
3. የአራዳ ቃላት በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን የአገልግሎት ስርጭት መግለፅ ፡፡
4. በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች እየተጠቀሙት የሚገኘውን የአራዳ ቃላት አፈጣጠር ማዘርዘር፡፡

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄ

***የዚህ ጥናት መሪ ጥያቄ የሚሆነው*** የተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ከቋንቋ ትምህርት አላማ አንፃር ሲመረመሩ ቃላቱ በሚደበኛው የተግባቦት ሂደት ላይ የሚፈጥሩት ክፍተት አለን? ***የሚል ሲሆን ንዑሳን መሪ ጥያቄዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡***

1. የአራዳ ቃላት ተለዋዋጩት በተማሪዎቹ ተግባቦት ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖ አላቸው?
2. የአራዳ ቃላት በተግባቦት ሂደት በየትኞቹ ክሂሎች ውስጥ ይታያሉ ?
3. የአራዳ ቃላት ለጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የአገልግሎት ስርጭቱ ምን ይመስላል?
4. በትምህርት ቤት ተማሪዎች እየተጠቀሙት ያለው የአራዳ ቃላት አፈጣጠር ምን ይመስላል?

አጥኚው መረጃዎችን በመመርመር ለነዚህ ጥያቄዎች በመረጃ ላይ ተመስርቶ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በአግባቡ ከተጠናቀቀ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡-

ሀ. የአራዳ ቃላት በተግባቦት ሂደት ላይ የሚፈጥሩትን ተጽእኖ በሚረዳት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ጥሩ የተግባቦት ክሂል እንዲኖራቸው እና ምን ማድረግ እንዳለበት

ያሚያከታል፡፡

ለ. አማርኛን በማስተማር ስራ ለተሰማሩ መምህራን የአራዳ ቃላት በተማሪዎች የተግባቦት ክሂል ላይ የሚፈጥረውን ክፍተት በሚረዳት የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመቀየስ ይረዳል፡፡

ሐ. የአራዳ ቃላት በተግባቦት ሂደት ላይ የሚፈጥሩትን ተጽእኖ በሚረዳት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ጥሩ የተግባቦት ክሂል እንዲኖራቸው እና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያሚያከታል፡፡

መ. ወደፊት በማስኩ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ፍተሻ በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ በተመረጡ አራት የመጀመሪያ ሁለተኛ ደረጃ እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎችን በናሙና በመውሰድ የሚደረግ ነው፡ክፍለ ከተማው የተመረጠው በቀላል የእጣ ናሙና ሲሆን አራት የመጀመሪያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤትን አካቷል፡፡ከተጠቀሱት የክፍለ ከተማው ትምህርት ቤቶች ውጭ ያሉትን የግልና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ጥናቱ አያካትትም፡ጥናቱም ከተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ከአማርኛ ቋንቋ ከመማር ግርና ከማፈ ውጭ ያሉትን ተላውጦዎች አይመለከትም፡ዋንኛ ትኩረቱም ተማሪዎቹ የአራዳ ቃላት አጠቃቀምን መሞምና ተንትኖ በሚደበኛው የተግባቦት ሂደት የሚፈጥረውን ክፍተት በማጠቆም ከአማርኛ ትምህርት አላማ አንፃር የመፍትሔ ሀሳብ መጠቆት ነው፡

## 1.7 የጥናቱ ተግዳሮቶች

አጥኚው ይህንን ጥናት ለማጥናት በሚንቀሳቀስበት ወቅት ካጋጠሙት ተግዳሮቶች መካከል እንደ ዋናነት ለመጥቀስ ያህል ለዚህ ርዕሰ ጉዳይ አጥጋቢ የሆነ ጥናት ማግኘት አለመቻሉ፡ የተጠኑትም ጥናቶች የጎዳና ተዳዳሪዎች የአራዳ ቃላት አፈጣጠርና አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ለሁለተኛ ዲግሪ ጥናት በበቂ ሁኔታ መረጃ የሚሰጡ አይደሉም፡በመሆኑም አጥኚው በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የራሱን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ካለው ውስጣዊ ተነሳሽነት የተነሳ ጥረቱን አሳርፏል፡፡

## 1.8. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

**የአራዳ ቋንቋ** – በንግግር ማህበረሰብ ውስጥ በማንኛውም ሰው ጥቅም ላይ የሚውል ኢ-መደበኛ ቋንቋ አጠቃቀምን፣ተራ ቋንቋ፣ለጽሁፍ ያልዋለ፣የምስጢር ቋንቋ፣የአንድ ቡድን ቋንቋ የሚል ፍቺ ሲኖረው በዚህ ጥናት የአራዳ ቃላት የሚለውን ትርጓሜ ይወክላል፡፡

የጓዳ ቋንቋ-(Jargon) በአንድ በተወሰነና ስዉር የስራ ክልል ዉስጥ ለሚሰሩበት ሙያና

በዚያው አካባቢ በሚገኙ ደርጊቶች እንደ መገለጫ አደርገው የሚጠቀሙበት

የቋንቋ ትርጉም ይዉክላል፡፡ (ለምሳሌ ሐኪሞች ፣የፋብሪካ ሰራተኞች፣ ምህንድስና፣

ሸማ፣ግብርና፣ ዉትርደና ወዘተ.)

ወጣት- የአራዳ ቃላት ሚጃ የተገኙት ከህፃናትና ወጣት ተማሪዎች በሚሆኑ ትርጉሙ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀዉ የእድሜ ክልል ለማመልከት አለመሆኑን ይገልፃል፡፡የወፍ ቋንቋ (Argote)-ይህ መግባቢያ በተወሰኑ የሀብረተሰብ ክፍሎች በሚስጥር ባሉ ወገኖች /ቡድኖች/ ዘንድ አገልግሎት የሚሰጡ የአራዳ ቃላትን ትርጉም ብቻ ይወክላል፡፡(ምሳሌ -የሌቦች፣የጎዳና ላይ ነጋዴዎች… ወዘተ.)

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናትና የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

### 2.1. የአራዳ ቃላት ምንነት

የተለያዩ መዝገበ ቃላቶችና የቋንቋ መጽሀፍት ስለአራዳ ቃላት ብዙም ልዩነት ባልታየበት መልኩ ብያኔ ሰጥተዉበታል፡፡ ከዚህ ዉስጥ ለምሳሌ ሁለቱን ለመጥቀስ የአራዳ ቃላት አዲስ በሚፈጠሩና በሚሰሩ ቃላት የሚፈጠር ለወጣቶች ወይም ደግሞ ለአንድ ማህበረሰብ ክፍል ግልጋሎት የሚሰጥ የንግግር ክፍል ሲሆን ዋና አላማዉም ለዚያ ቡድን ምስጢር በሚደበቅ በመግባቢያነት ማገልገል ነው Hartman (1976፣210)፡፡ከዚህም በተጨማሪ The Cambridge Encyclopedia of language (1996፣1349) ደግሞ እንዲህ ሲል ይበይነዋል የአራዳ ቃላት/Slang/ ኢ-መደበኛ የሆነ ቋንቋ ሲሆን ትሁት ያልሆኑ ቃላትና ትርጉሞችን እንዲሁም አባባሎችን ሊጨምር የሚችልና ለአጭር ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚዉል መግባቢያ ሲሆን አገልግሎት የሚሰጠዉም እርስ በእርስ በሚተዋወቁ የተወሰኑ ማህበራዊ ቡድኖች መካከል ነው፡

ቀደም ሲል እንዳየነው የአራዳ ቃላት በሁሉም ቋንቋዎች ዉስጥ ሊኖር የሚችል የቋንቋ አጠቃቀም ክፍል እንደሆነ እና በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ ብያኔዎች እናገኛለን እነዚህ ብያኔዎች በብዙ መልክ የሚመሳሰሉ ቢሆኑም ከቃላቱ ተጠቃሚ የመኖሪያ ክልል፣በህብረተሰቡ የእድገት ደረጃ ማእያየት ወዘተ. የተነሳ ልዩነት ይኖረዋል፡፡ሆኖም የአራዳ ቃላት በአገልግሎት ላይ የሚቆይበትን ጊዜ የተጠቃሚዎቹን ሁኔታ ብዙት የሚያሳዩትን ባህሪያትና አጠቃቀም በመመርኮዝ ብያኔ ለመስጠት አያስቸግርም፡ይህንንም ሀሳብ ምትኩ (1983) እንደሚከተለው ያጠናክረዋል፡፡አራደኛ የሰዋሰዉ ስርአት የሚከተል ሰዎች ከሚግባበበት

የቋንቋ ህግ ያፈነገጠ በአንድ ቃል ወይም በቃላት ደምሮ ሀሳብ የሚለጽበት እንደሆነና አንዳንደም በተሜሏ ወይም በከፊል አረፍተ ነገር አባባሉን እንደሚያስወብው ይጠቅስና ከዚህም በተጨሜሪ የአራዳ ቃላት የግለሰቦች የህይወት ክፍል መሆኑንና የህብረተሰብን ታሪክ እንደሚያንፀባርቅ ይገልፃል::

እንደ አብነት (2007) አገላለፅ የአራዳ ቃላት በንግግር ውስጥ በማህበረሰቡ ጥቅም ላይ የሚዉል ኢ-ሜደበኛ የቃላት አጠቃቀምን አራዳ ቋንቋ ይለዋል፡፡Hartman (1976)ሜደበኛ ያልሆነ ቋንቋ የምንለው ከሜደበኛ ቋንቋ ለየት ያለ አነባብ፣የሰዋስው አጠቃቀም፣የቃላት ምጥረታ የሚታይበት የቋንቋ ሜልክ ነው፣ከቅርብ ጓደኞቻችንና በብዘት አብረውን ከሚዉሉ ሰዎች ጋር በምነጋገርበት ጊዜ የምንጠቀምበት መሆኑን ገልጿል፡፡

## 2.2. የሜደበኛ ቋንቋ ስያሜ

ቋንቋን መፍጠርም ሆነ የመጠቀም ችሎታ ያለው የሰው ልጅ ብቻ ነው፣የቋንቋ አጀማመርም ከሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ጋር እኩል የሚሄል እድሜ አለው፣በተለይ የንግግር ቋንቋ ታሪክ በጣም እሩቅ ዘመን ነው፣የጽህፈት ቋንቋም ቢሆን ከጥቂትና ስዕላዊ መግለጫ ተነስቶ ዛሬ ክፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ይህ የሰው ልጅ ልዩ ተሰጥኦ የሆነው ቋንቋ የሰውን ልጅ ትልቅ የአስተሳሰብ ችሎታና የፈጠራ ብቃት አጉልቶ የሚያሳይ ነው፣ሰው ቋንቋን የሀሳብ መግለጫ የእርስ በእርስ መግባቢያ መሳሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡

Hartman(1976) የተባለው የቋንቋ ተመራማሪ ሲገልጽ "ቋንቋ በጣም ዋና እና ተቀዳሚ ከሚባሉት የሰው ልጅ ባህሪዎች ውስጥ አንዱ ነው፤ቋንቋን አመጭ ወደሆነ ሀሳብ መግለጫ መግባቢያ መሳሪያነት የማሳደግ ሂደት ምንአልባትም ትልቁ የሰው ልጅ ስኬት ነው፡ በዓለም ላይ በሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ ቋንቋዎች አሉ፣እነዚህም ቋንቋዎች የራሳቸው የሆነ ቅርፅ፣አገባብና መዋቅር አላቸው፣አንዱን ቋንቋ እራሱን ብቻ እንኳ ብናይ የተለያዩ ልዩነቶች ይኖሩታል፡፡ለምሳሌ አንድ ቋንቋ የተለያዩ ዘየዎች እና ሜደበኛ ያልሆነ አጠቃቀም ይኖረዋል፡፡ዘየዎቹ በራሳቸው በሶስት ይከፈላሉ ግለ-ዘየ ከግለሰብ ግለሰብ የሚለያይ የቋንቋ አጠቃቀም፣ማህበራዊ ዘየ በማህበራዊ ዳራ /ቦታ/ ልዩነት ምክንያት የሚፈጠር ዘየና አካባባዊ ዘየ በቦታ ርቀት ምክንያት የሚፈጠር የአነጋገር ልዩነት ናቸው Hartman (1976) ::''

እንደ ሰለሞን፣(1997) እና አስቴር፣(2000) ሜደበኛ፣ቃላት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ከሞላ ጎደል የሚያሟሉ ናቸው፣በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ሁሉ እኩል ስርጭት ሊኖራቸው አይችልም፣አንዳንዶቹ በተደጋጋሚ በብዙ ቦታዎች ስራ ላይ የሚዉሉ ናቸው፣አንዳንዶቹ ግን አይደሉም፣በከተማም ሆነ በገጠር ተዘውትረው የሚሰራባቸው በስርጭት የተለያዩ ናቸው፣ሜደበኛ ቃላትን ምሁራን እንደሚከተለው ይበይኑታል፤ቃል በአንደበት ወይም በፊደል ምልክትነት የሚለፅ ሃሳብ ወይም የስሜት ውክይ ነው (ዳኛቸው፣1988)፡፡ይህንን ሃሳብ ደረጀ (1996) ሲያብራራው አንደን ሀሳብ በደርሰት ሜልክ ለመፃፍ ወይም በንግግር አቀነባብሮ ለማቅረብ የሚቻለው ሀሳቡን እንደታሰበው አደርገው የሚያስተላልፉ ማሳረታዊ

ቃላትን ማምረጥ ሲቻል ነው፡ከላይ የተገለፀው የቃላት ስያሜ የሚወክለው ሚደበኛ ቃላትን ነው፡ይህ ጉዳይ ለሚደበኛነት እንደ አንድ ማሳኪያ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡በሌላ በኩል ጋዜጣ ፣ሬዲዮ፣ቴሌቪዢን፣ወዘተ.የመሳሰሉት የህትመትም ሆኑ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ቃላትም ሚደበኛ ሊባሉ ይችላሉ፡ከዚህ በተጨማሪም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ለትምህርት ማስጫ መቀበያ የሚያገለግሉ እንዲሁም በማግስት ማስሪያ ቤቶች፣ህዝባዊና ልማታዊ ድርጊቶች ወዘተ…ለስራ ማስሪያነት የሚያገለግሉ ቃላትን ሚደበኛ ብለው ይፈርጃሉ፡Yule(1996፣180-190) የአንድን ቋንቋ የተለያዩ ሜልኮች /አይነቶች/ በሚሚለከት <<የቋንቋ ጥናት>> በሚለው መጽሐፉ ሲያስረዳ፡ - አብዛኛውን ጊዜ በአንድ የተወሰኑ የቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋውን በአንድ አይነት ሜልኩ እንደሚጠቀሙ እውቅታውን በብዘት አያስተውሉም፡፡

አንድ ቋንቋ በተለይ በሚነገርበት ጊዜ ከአንድ በላይ ሜልክ ሊይዝ ማቻሉን እንገነዘብም Yule(1996፣227)፡፡በቋንቋ የተለያዩ አጠቃቀሞች ልዩነት የሚታየው በዘየዎች ብቻ አይደለም፤አንድ ቋንቋ ሚደበኛና ሚደበኛ ያልሆነ አጠቃቀሞች /ሜልኮች/ አሉት፡፡ ሚደበኛ ቋንቋ የምንለው በሚደበኛነት ለብዜራዊ መግባቢያነት የሚውለውን፣በጽሁፍ ሜልክ በጋዜጦችና በመጽሀፍት ተጽፎ የሚቀርበውን እንዲሁም በትምህርት ቤቶችና በማናኛ ብዙሀን አማክኝነት ለህዝብ የሚደርሰውን ቋንቋ ነው፡ ይህ የቋንቋ ዘርፍ በህብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ ግምት የሚሰጠውና ተቀባይነት ያለው መሆኑን ሲናገር Hartman(1976) የሚደበኛውን ቋንቋ ብያኔና በብዘትም ከማገር ይልቅ በማፍ ሜልክ የሚቀርብ መሆኑን እንደሚተለው አስቀምጧል፡፡ ሚደበኛ የምንለው ቋንቋ፣ቋንቋውን መማር ለሚፈልጉ የምናስተምረው አይነት ነው፡የዚህ አይነት ቋንቋ በትምህርትና በማናኛ ብዙሀን አማክኝነት ለህዝብ የሚቀርብ ሲሆን ከንግግር ይልቅ በቀላሉ በጽሁፍ ሜልክ የሚገለጽ ነውYule(1996፣227)፡፡ሚደበኛ ያልሆነ ቋንቋ የምንለው ከሚደበኛ ቋንቋ ለየት ያለ አነባበብ፣የሰዋስው አጠቃቀም የቃላት ምስረታ የሚታይበት የቋንቋ ሜልክ ነው ከቅርብ ጓደኞቻችንና በብዘት አብረውን ከሚውሉ ሰዎች ጋር በምነጋገርበት ጊዜ የምንጠቀመው በአብዛኛው የዚህ አይነቱ ቋንቋ ነው (Hartman፣1976) ይላል፡፡

## 2.3. የኢ- ሚደበኛ ቋንቋ ስያሜ

ለኢ-ሚደበኛ ቃላት አልፎ አልፎ በንግግር ጊዜ የምንጠቀማቸው ሲሆኑ የቋንቋው ተናጋሪ በሙሉ የማያውቃቸው በተወሰኑ አካባቢ ተናጋሪዎችና በተወሰነ ክልል ብቻ የሚታወቁ ናቸው፡ሚደበኛ ባልሆነው የቋንቋ ሜልክ ስር የሚጠቃለሉ ብዙ የቋንቋ ዘርፎች አሉ፡ከነዚህ ውስጥ በእንግሊዘኛው <<ስላንግ >> ወይም አርጎት እና ጃርገን የሚባሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡የአራዳ ቃላት ራሱን ችሎ የሚነገር፣ለሚደበኛ ጽሁፍ ስራ የሚውል፣በሚደበኛ ቋንቋ ላይ ጥገኛ በመሆን ጣልቃ እየገባ የሚነገር በመሆኑና ራሱን የቻለ አገባብና የሰዋሰው ስርዓት የሌለው ሲሆን ቃላቱም በአንድ ቋንቋ ላይ ብቻ የሚወሰኑ አይደሉም፡የተለያዩ ቃላትን /ከአካባቢው የተለያዩ ቋንቋዎች/ ተቀላቅለው እናገኛቸዋለን፡፡ከዚህ በተጨማሪም የአራዳ ቃላት

ተጠቃሚዎች የመደበኛውን ቋንቋ ቃላት በማስጠር፣በማስረዘም የቃሉን ሆሄያት ከግራ ወደ ቀኝ በማስቀመጥ መግባቢያ ይፈጥራሉ የአራዳ ቃላት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን የተወሰኑ ማህበራዊ ክፍሎች የሚያገናኝ፣ለጋራ መግባቢያነት ያልበቃ ከተለያዩ ቋንቋዎች ቅንጭብጭብ ቃላቶች የተሰናደረ በጽሁፍ ያልዋለ፣የምስጢር መልዕክት ማስተላለፊያ መግባቢያ ነው (Hartman፣1976)፡፡

አገልግሎታቸው በተወሰኑ ሰዎች አካባቢ የተገደበ ሲሆን ቃላቱ በሁሉም የቋንቋው ተናጋሪ የማይታወቁ ከመሆናቸው አንፃር በመግባባት ሂደት መልዕክትን ሊያደበዝዙ ይችላሉ (አስቴር፣2000) በማለት ትገልፃቸዋለች፡፡ከዚህም በማስከተል በኢ-መደበኛ ቃላት ስር መደበኛ ባልሆነው የቋንቋ መልክ ስር የሚካተቱ ብዙ የቋንቋ ዘርፎች አሉ እነዚህም ዘዬ፣የአራዳ ቃላት፣የሙያ (የስራ አካባቢ) ቃላት፣የባዕድ (የተውሶ) ቃላት፣ቀበልኛ እና ፀያፍ በማለት ከፍለዋቸዋል (ሰለሞን፣1997) እና (አስቴር፣2000)፡፡የነዚህ ቃላት ተጠቃሚዎች በከተማ የሚኖሩ ወጣቶች ሲሆኑ ወጣቶቹ ተማሪዎች፣ሌቦች፣የጎዳና ተዳዳሪዎች፣የታክሲ ረዳቶች የጎዳና ላይ ነጋዴዎች ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ፡፡እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች አራደኛ ቃላትን የሚጠቀሙባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ምስጢር ለመደበቅ፣ዘመናዊ መስሎ ለመታየት ወዘተ.ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሌባው ከፖሊስ፣የታክሲ ረዳቱ ከተሳፋሪ፣የጎዳና ተዳዳሪው ከእግር መንገደኛ ወዘተ.ምስጢር ለመሰወር የሚጠቀሙባቸውን ቃላት መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ለምሳሌ ያህል በአማርኛ ጥሩ ነው ለማለት ሜጋ አለው፤ቆንጆ ነች ለማለት በርድ ነች፣ሄደ ለማለት ሚሸ፣ ሞተ ለማለት ጫፈ፣እና ወዳጄ ነች ለማለት ኪካውነች የሚሉ አገላለፆች ለአራዳ ቃላት ምሳሌ እንደሚሆኑ (አብነት፣2007፣210)ይገልፃል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ(ሰለሞን፣1997፡46) ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት እንደ አስረጂ በመውሰድ ይገልፃል፡፡

| **ቃል** | **ፍቺ** |
|---|---|
| ሀ. ዛፓ | ፖሊስ |
| ለ. ሴሎ | ጠላ |
| ሐ. ቢጫ | ጠጅ |
| መ. እንባ | ተቆርቋሪ |
| ሠ. ጀለስ | ጓደኛ |

ረ. ፍንዳታ                  አፍላ ወጣት

## 2.4. የአራዳ ቃላት በማን ተፈጠሩ?

ሁሉም ቋንቋ በሚልእክት ማስተላለፊያ በሀሳብ መግለጫ መሳሪያነቱ ተመሳሳይ ቢሆንም እያንዳንዱ ቋንቋ እንደተጠቃሚው አኗኗር ባህል የእድገት ደረጃ ወዘተ. ልዩነት በስርአትና በአገልግሎቱም ይለያያል፡፡ እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ የሆነ የድምፅ፣የቃላትና የሰዋስው ወዘተ. ስርአት ያለው በመሆኑ ማለያ አለው:: እንዲሁም እንደ አገራችን ባሉ ልሳነ ብዙ አገሮች ሁሉም ቋንቋዎች እኩል የሆነ አገልግሎት አይኖራቸውም፡ አንዱ በጋራ መግባቢያነት፣በስራ ቋንቋነት፣በማስተማሪያ ቋንቋነት ወዘተ. ሲያገለግል ሌላው ደግሞ የሀይማኖት ማስበኪያ ወይም የተወሰኑ ማህበራዊ ቡድኖች መግባቢያ ሊሆን ይችላል፡፡በዚህም መሰረት ህብረተሰቡ በየትኛው ቋንቋ የት፣መቼና ከማን ጋር እንደሚለገሉበት ለይቶ ያውቃል፡፡ስለአንድ ቋንቋ ማጥናት ስንፈልግም በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚከሰተውን የአጠቃቀም ልዩነት እንገነዘባለን፡፡ እንደምንገልፀው የሀሳብ ልዩነት የቋንቋ አጠቃቀማችንም ይለያያል፡፡ከአዛውንቶች፣ከልጆቻችን፣ ከስራ አለቆቻችን፣ከጓደኞቻችን በትምህርት ክፍል ውስጥ፣የቋንቋ አጠቃቀማችን ይለያያል፡፡ በአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ ህብረተሰብ ውስጥ በሙያ፣በእድሜ በሚልክአ- ምድር ልዩነት ወዘተ. ምክንያት የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም ያላቸው ማህበረሰባዊ ቡድኖች መኖራቸው ግልጽ ነው Leslau( 1964፣7)፡፡

ባዬ (1976፣2) የቋንቋ አጠቃቀምን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ያጠናክረዋል‹‹…በከተሞች የሚነገረው አማርኛ ይሁን ሌላ ቋንቋ በገጠር ከሚነገረው ሚልኩ እያደረ የተለየ ይሆናል፡፡ምን ያህል እንደሚለይ ምንአልባት ከተማው ለገጠሬው ተናጋሪ፣ገጠሬው ደግሞ ለከተማው ካለው አመለካከት ማግኘት ይቻላል፡፡ዛሬ የገጠር አማርኛ፣የከተማ አማርኛ ከከተማውም የአራዳ አማርኛ የሚባሉት ሁሉ የሚታወቁት ይህንኑ ነው ፡፡››

ከህብረተሰቡ ተገንጥሎ ለብቻው የሚኖር ሰው የለም፡ቡድኑም በርካታ አባላትን ያቀፈ ወይም በተወሰነ ክልል ውስጥ በሚገኙ ጥቂት ሰዎች የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡እነዚህ የህብረተሰብ የቋንቋ ቡድኖች (speech community) ናቸው፡የአራዳ ቃላትንም በርካታ ማህበራዊ ቡድኖች ለተለያየ አገልግሎት የሚያውሉት የቃላት አጠቃቀም ውስጥ አንዱ ነው፡የአራዳ ቃላት ልዩልዩ ቡድኖች ከሚለገሉባቸው የቋንቋ አይነቶች መካከል አንዱና ሰፊ ግልጋሎት የሚሰጥ ነው፡የአራዳ ቃላት በማናቸውም ቋንቋዎች ውስጥ ሊገኝ የሚችል ነው::

ማንኛውም ማህበራዊ ቡድን የራሱን መግባቢያ ወይም የጓዳ ቋንቋ ሊፈጥር ይችላል፡፡ይህ በጣም ውስን በሆነ አካባቢና በሰዎች አመካኝነት የሚፈጠረው የጓዳ ቋንቋም እየሰፋ ሲሄድ ወደ ስላንግ ወይም አርጎት ይለወጣል በማለት Leslau(1964፣6) ይገልፃል፡፡በአጠቃላይ ይህም ቋንቋ በፍጥነት በመቀመጥ ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንደዋና መግባቢያና ምስጢር መደበቂያ ሊሆን ይችላል፡፡ ምስጢር መደበቅ

ደግሞ የስላንግ ወይም አርጎት ዋናና ተቀዳሚ አላማ ነው አርጎት ጥቅም ላይ የሚውለው በአንድ ሙያዊ ቡድኖች ወይም ደግሞ ምስጢራዊ የሆኑ ህብረተሰቦች በሚሆኑ በንግግር ወቅት ከነዚህ ክፍሎች ውጪ ያሉት ሰዎች እንዲያውቁት ወይም እንዲገነዘቡት አይጠበቅም Leslau(1964፣7)፡፡በአጠቃላይ የዚህ የቋንቋ አገልግሎት ለተወሰኑ ማህበረሰብ ክፍሎች ብቻ የሚያገለግል ቃላቶቹም ሆኑ አባባሎቹ ከሚደበኛው ቋንቋ ትንሽ ፈንገጥ የሚል፣ ለማስፋፋትም ሆነ ለማጥፋት ፈጣን የሆነ ለማያውቀው ሰው በቀላሉ የማይገባ፣ ምስጢር ለሚደበቅ የሚጠቅም፣ረጅም አባባሎችን አጭሮና ለተጠቃሚዎች በቀላሉ በሚገቡ ቃላት የሚነገ የመግባቢያ አይነት ነው ባዬ(1976)፡፡

በአንድ ህዝብ ውስጥ ያለውን ቅቡል አስተሳሰብ፣ባህል፣ልማድና ወግ እንዳለ ከመቀበልና ከማፀባረቅ ለየት ያልውንና ያልተለመደውን ባህል አንድም ከማየት፣አንድም ደግሞ ከተለያዩ ማናኛ ዘደዎች ከሚቀስሙት አስተሳሰባቸውን በማለወጥ የራሳቸው የሆነውን ባህል መቀበልና ለሰም ተገዥ መሆንን እንደኋላ ቀርነት አደርገው ስለሚያለከቱት ነው (ምትኩ፣1983) ፡፡

የአራዳ ቃላት አፈጣጠር በሚያለከት Leslau(1964፣8) የቃላቱ ማኛ ስርው–ቃል ወደ ተለያዩ ሚልኮች የተቀየሩ የሚደበኛውን ቋንቋ ቃላት ወይም ደግሞ ከሌሎች ቋንቋዎች በውሰት የተገኙ ናቸው፡አንዳንድ ጊዜም የሚደበኛውን ቋንቋ ቃላት እንዳሉ ከወሰዱ በኋላ ሚደበኛ ትርጉማቸውን በመቀየር የራሳቸው የሆነ ለየት ያለ ትርጉም እንዲይዙ ያደርጓቸዋል፡፡የአራዳ ቃላት በብዛት የሚገኙት በውሰት ነው፡በዙሪያቸው ከሚገኙ የተለያዩ ቋንቋዎች አጭር፣አማኛና ሀሳብን በተገቢው መንገድ የሚገልጹ ቃላትን ይወስዳሉ፡፡እያንዳንዱ አርጎት በሚያውሰው ቋንቋ ባህሪና ሚልካ ምድራዊ አቀማመጥ መሰረት ቃላትን ይዋሳል Leslau (1964፣13)፡፡ይህም ማለት ለውሰቱ በአካባቢ የሚገኘው ቋንቋ ባህሪና አቀማመጥ ስርጭት ይወስነዋል ማለት ነው፡ስለ አራዳ ቃላት አፈጣጠር ይህን ያክል ካልን አሁን ደግሞ የአራዳ ቃላት ተጠቃሚ ማህበራዊ ቡድኖች ለምን የተለየ ቃላት እንደሚፈጥሩ እንሚልከት፡ – እነዚህ ቡድኖች የአራዳ ቃላት ለመጠቀም የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው፡ክልክል የሆኑ ስራዎችን በድብቅ ለመስራት ወደ ስርቆት በሚሰማሩበት ጊዜ፣ የተበላሹ እቃዎችን በማታለል ለመሸጥ ሲሉ ልዩ ልዩ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡ከዚህ ሌላ በህብረተሰቡ ባህልና ወግ መሰረት እንደ ነውር የሚቆጠሩ አባባሎችን ወይም ድርጊቶችን በቀጥታ ከመናገር ወይም ከማለት ይልቅ የእነሱ ቡድን አባል ያልሆነ ሰው እንዳያውቅባቸው ለየት ባለ ቋንቋቸው ይግባባሉ(Leslau፣1964)፡፡

ማንኛውም የአንድ ማህበረሰብ ክፍል የራሱን የስራ ቦታ መግባቢያ ለፈጥር ይችላል፤ይህም መግባቢያ እያደገና እየሰፋ ሲሄድ ስላንግ ይሆናል፡፡ከነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ታዳጊዎች፣የጎዳና ላይ ሰራተኞች፣ወታደሮች፣የእጽ ተጠቃሚዎች፣ሌቦች በብዛት ስላንግን የሚፈጥሩ ቡድኖች ናቸው፡Harold & Flexner (1967፣6) የአራዳ ቃላት አገልግሎቱ ምስጢር ሚደበቅ ብቻ አይደለም፡፡እነዚህ ክፍሎች ለቡድናቸው ከፍ ያለ ግምት ለማስጠት፣ከሌሎች ማህበራዊ ክፍሎች ለማለየት፣ለማዝናናት ተሰብስበው

በሚጫወቱበት ጊዜ እና ሌሎች ማህበራዊ ክንውኖች ከመደበኛው ቋንቋ ይልቅ ለየት ያለ ቋንቋን ማጠቀም ይፈልጋሉ፡፡ (Yule፣1996) ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር የእነዚህ ንዑሳን ቡድኖች አባላት መደበኛ ያልሆኑ የቋንቋ አይነቶችን ማጠቀም የቡድናቸውን ማህበራዊ ትስስር አንድነት ለማጠናከር አይነተኛ ማገድ አደርገው ይወስዱታል ከዚህ በተጨማሪም ይህ ቋንቋ ያልተንዛዛና አጭር በመሆኑ በተጠቃሚዎቹ ተመራጭ ት ይኖረዋል ምክንያቱም ከምስጢራዊ መግባቢያነት ሌላ የአራዳ ቃላት ጠቀሜታ ለሚጠቀምበት ማህበራዊ ክፍል የተለያዩ ግልጋሎት ይሰጣል፣ያዝናናል፣የስነ ልቦና እፎይታ ያስገኛል፤ከሌላው በልጦ ለመታየት ያበቃል፤ከተሜ ያሰኛል በማለት ይገልፃል፡፡

ሁል ጊዜ የቋንቋ አጠቃቀማችን ተመሳሳይ አይደለም፡እንደ አካባቢውና ሁኔታው ይለያያል ልዩነቱም የቃላት፣የመዋቅርና የአነጋገር ቃና ሊሆን ይችላል፡፡ለምሳሌ መጥፎ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ለመግለፅ ስንፈልግ መጥፎ ቃላት እንደምንጠቀም ሁሉ በመደበኛ ወይም ህዝባዊ ንግግሮች ላይ የቃላት ምርጫችንና የአነጋገር ስልታችን ልዩነት እንዳላቸው Bender(1976፣185) ይጠቁማል፡፡በቋንቋ አጠቃቀም ለውጥ ውስጥ ከሚደረገው ለውጥ በተጨማሪ አንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ እንደሚለወጥ በሚከተለው አባበል ተመልክቷል በንግግራችን ውስጥ የሚታየው የቃላት፣የመዋቅርና የአነጋገር ቃና ለውጦች ብቻ ሳይሆኑ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የሚደረግ ለውጥም አለ Bender (1976፣185)፡፡

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ልክ ከማገር ወደ ማፍ ተግባር ስንገባ የቋንቋ አጠቃቀም ለውጥ እንደምናደርገው ሁሉ ከአንድ የማገር ሁኔታ ወደ ሌላ የማገር ሁኔታ ከገባን የቋንቋ አጠቃቀማችን በውስጡ ሊከሰቱ ከሚችሉ ለውጦች ባሻገር ቋንቋውን ወደ ሌላ ቋንቋ እንደምንለውጠው ነው፡ ይህም ከሰው ልጅ ቋንቋ የተወሰነ ግብ ተስማሚ በማድረግ የመጠቀም ችሎታ የመነጨ ነው፡ቋንቋ የሰውን እንቅስቃሴ ድርጊት የመግለጽ አቅም እንዳለው ሁሉ የሰው ልጅም ቋንቋን ከሁኔታዎች ጋር አጣጥሞ ሁኔታውን በአግባቡ እንዲገልጽ ያደርገዋል የአራዳ ቃላት ከዚህ ፍላጎት አንፃር የተፈጠረ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡

የአራዳ ቃላት የቡድን አጠቃቀም በመሆኑ እነዚህ ቡድኖች ለሚጥሟቸው አዳዲስ ገጠሞቻቸውን ለመቋቋም ወይም አዲስ ሀሳብ በመፍለቅ የተለየ ተግባር ለሚፈፅም ከማህበረሰቡ ቀድመው አዲስ አጠቃቀምን ይፈጥራሉ፡ለአዲስ ገጠሞች አዲስ ቃላት ለመፍጠር የቡድኑ አባላት ብዛትና በቡድኑ መካከል የሚደረገው ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ወሳኝነት እንዳለው kottler (1967፣231-240) ይናገራል፡፡ሰው በቋንቋ የመጠቀም ችሎታ ያለው መሆኑን የሚከተለው ጥቅስ ያረጋግጣል፡፡በቋንቋችን፣ አእምሮአዊ ምክላችን፣ በእኛና በሌሎች አእምሮ ውስጥ ሁልግዜ እንደገና እንፈጥራለን፡፡የዚህ ምክል የተወሰነው ክፍል ...በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ የመጥፎ ቋንቋዎችን በመጠቀሙ ቡድኖች ሲፈጠር ቀሪው በእኛ የመደበኛና የኢ-መደበኛ ቃላት ምርጫምክንያት የሚፈጠር ነው kottler (1967፣197) ፡፡

እንደ ቋንቋው የአጠቃቀም ልዩነት ሁሉ በተለለያዩ አካባቢዎች በአሚኛ የሚገሩ የአራዳ ቃላትም ሙሉ በሙሉ የተለያዩ ናቸው ባይባልም ያገኛኘታቸውና የተገኘበት ቋንቋ ትርጉም ውዘተ. ልዩነት

ይኖራቸዋል፡፡በተጨማሪም በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከውጭው አለም ጋር የእለት በእለት ግንኙነት ባለው የንግድ ማዕከል በሆነ አካባቢና በሌላው እንዲሁም በገጠርና በከተማ አካባቢ በሚኖሩ የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚዎች ዘንድ የሚሆየው የቃላት መፍጠር ዝንባሌና ለአዲስ ነገር የማለጡ ሁኔታ አንድ አይሆኑም በማለት ባዬ (1976) ይገልፃል ፡፡

ለዚህም ‹‹…ከተማች በተለይ ዋና ከተማች የብዙ ብሄረሰቦችና የቋንቋዎች መዲና ብቻ አይደሉም፡ከሁሉም በላይ ደግሞ ከውጭው አለም ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሚፀምባቸው ቦታዎች ናቸው፡ስለሆነም ብዙ አዳዲስ ሁኔታዎች፣ደርጊቶች፣ክስተቶችና ግንኙነቶች ከሌሎች ቦታዎች ይልቅ በነሱ ይፈጠራሉ፡ስለዚህም ብዙ ቃላት በፈጠራም ሆነ በውሶት የሚሆዩት በነዚህ ቦታዎች ነው፡የፋብሪካ ሰራተኞች ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ብቻ የሚግባበቡበት ሲሆን ከዚህ የምንረዳው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ለሚሆይው የቃላትና የአጠቃቀም ልዩነት የተናጋሪው ህብረተሰብ ልዩ ልዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ትልቁን ስፍራ ያማክታል፡፡ ዝኒከማሁ(1976 ዓ.ም)

ከዚህ የምንረዳው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ለሚሆየው የቃላትና የአጠቃቀም ልዩነት የተናጋሪው ህብረተሰብ ልዩ ልዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ትልቁን ስፍራ እንደሚሆዝ ሲሆን፤ለአራዳ ቃላት ማብዛትም የአካባቢው ሁኔታ ወሳኝ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 2.5. የአራዳ ቃላት ባህሪያት

የአራዳ ቃላት የተለያየ ባህሪያትን የሚያንጸባርቁ ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ –

**1.** ዘመናዊነትን /ወቅታዊነትን/ ማንየት አንዱ ባህሪያቸው ነው፡ይህ ማለት በወቅቱ የሚከሰተውን አዲስ ክስተት ለመግለፅ እንግዳ ወይም አዲስ ቃልን መፍጠር ባህሪ አለው፡ ቀደም ሲል ላልነበረ ወይም ላልተለመደ ግኝት አዲስ ቃል መፍጠር አማራጭ የሌለው ሲሆን የአራዳ ቋንቋ ግን ቀደም ሲል ለሚታወቅ ጉዳይ ብቻ ሣይሆን አዲስ ቃል የሚጥረው ስያሜ ኖሮትም በጊዜው አዲስ ክስተት ካጋጠም ተጨማሪ አዲስ ቃል እንዲመጭ ያደርጋል ምትኩ(1983)፡፡

2. ቃላቱ ለዘወትር ግልጋሎት ከምንጠቀምባቸው ይበልጥ ከነ–ጥበባዊ ቀለም ያላቸውና ወደ ዘይቤያዊነት የሚያደሉ ናቸው፡ከነዚህ ቃላት ውስጥ ብዙዎቹ ጥሩ የአገላለጽ ለዛ ያላቸው ናቸው፡ ይህንን አስሚክቶ Comptons Encyclopedia ሲገልጽ የአራዳ ቋንቋ አገላለፆች አንዳንድ ጊዜ በአንድ አካባቢ የተወሰኑ ቢሆኑም የተዋጣላቸው ዘይቤያዊ ንግግሮች ናቸው Comptons encyclopedia(2012)፡፡ይህ ስውር ድብቅ መግባቢያ ከሌሎች መግባቢያዎች ልዩ የሚያደርጉት የራሱ የሆኑ ባህርያት ይኖሩታል የአራዳ ቃላትና አባባሎች ከአንድ ሁኔታ ይገኛሉ፣በወጣቱ አፍ እየተማለሱ ከገቡ ይለማሉ፡ለዘለቄታም የሚኖራቸው ጥቂቶች አይደሉም፡ሌሎች የአራዳ ቃላት ለተወሰነ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውሉና ይጠፋሉ፡አንዳንድ ቃላትና አባባል ደግሞ በኑረትና በሞት መካከል በመሆን ለብዙ ጊዜ ይታያሉ ለምሳሌ ከጥቂት አመታት በፊት"ጀጋ" የሚባው የአራዳ ቃል በወጣቱ ጠቀሜታነት ነበረው፡ቀስ

በቀስ ገሪባ፣ ጤፀ በማቅሰሉት የአራዳ ቃላት ቢተካም ፊት የነበረው ቃል ሙት በሙት አልጠፉም፡ ማኛውም ህያው ቃላት ለብዙ ጊዜ የቋሚት ባህሪ ይዘው ለማዝለቅ አይቻላቸውም፡ በዚህም አንፃር የአራዳ ቃላት ይፈጠራሉ፣ ይጠፋሉ፣ ለዚህ ደግሞ ምክንያት እያንዳንዱ ትውልድ ነባር ነገሮችን ለመግለጽ የአዲስ ቃላትና አባባል ለማቅየም ስለሚሹ ነው፡ የቃላቱ ተጠቃሚዎች በአንድ በኩል እርስ በእርሳቸው የተዋሀዱ በሌላ በኩል በቁጥር የበዛና ካለው ባህል ፈንገጥ ያሉ በመሆናቸው በየወቅቱ በብዛት እየተፈጠሩ ላሉት የአራዳ ቃላትና አባባል ተጠያቂ ናቸው፡ ተናጋሪዎቹ የተሰባሰቡ በመሆናቸው አንዱ ቃል ተፈጥሮ ሳይውል ሳያድር በአካባቢው ራሱን ያሳውቃል፣ ብዙም ሳይቆይ በሰፊው ይለመዳል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተለምዶ ግልጋሎት የሚሰጥ የአራዳ ቃል የሚደበኛው ቋንቋ ቃል ይሆናል፡፡

3. እንደማኛውም የቋንቋ ባህሪያት የአራዳ ቃላት በተለያዩ አጋጣሚዎች ከቀረቡት ቋንቋዎች ቃላትና ሐረጋትን መዋሱ ነው፡ ይህም ሲባል በአካባቢው የሚነገሩ ቋንቋዎች ካሉ ወይም ሊቀርቡት ከቻሉ ነው፡

4. ቡድናዊ መሆኑ የአራዳ ቃላት በጠቅላላው ሕብረተሰብ የሚነገር ሳይሆን በተወሰኑ ቡድኖች አካባቢ ብቻ የሚያገለግል ነው፡ ከአራዳ ቋንቋ ተጠቃሚ ቡድን ውጭ የሆኑት ሰዎች የሚናገሩትን ማንዘብ እንዳይችሉ ታስቦበት የሚደረግ ሲሆን በዚህም የፈለጉትን ምስጢር ሳይሰጉ ማስተላለፍ ይችላሉ፡ የሚያደርጉትን ወይም የሚናገሩትን ጉዳይ ምስጢር ለመጠበቅ በአራዳ ቃላት የሚጠቀሙ ውስን የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡

ከዚህም በተጨማሪ ዘለቀ (1977 ዓ.ም) ስለአራዳ ቋንቋ ቃላትና አባባል ሚፈጠርና ዘለቄታ ማግኘት ምክንያት ይሆናሉ ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ሶስት ምክንያቶች መቀንዘር ይቻላል፡፡

ሀ. ተጠቃሚው ክፍል አዳዲስ የአራዳ ቃላትን መጠቀሙ በመውጣቶች ዘንድ አራዳ ለመባል ስለሚያበቃ የተፈጠሩትንም ሆነ ፈጥረው ለመጠቀም ወደ ኋላ የሚሉ የሉም፡ ለአንድ ጽንሰ- ሀሳብ ከሁለትና ሶስት ቃላት በላይ መግለጫ ይሆናሉ፡ በዚህም በዚያም ብሎ የቋንቋው የቃላት ክምችት ክፍ ይላል፡፡

ለ. የአራዳ ቃላት ተጠቃሚዎች በብዛት በህብረተሰቡ ዘንድ ማግኘት ውጤቱ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር ከፍ ያለ ነው፡ ውጤቱ የአራዳ ቃላት ተጠቃሚ እንደመሆኑ ለቃላቱ ሚፈጠርና ዘለቄታ ማግኘት ወሳኝ ይሆናል፡፡

ሐ. በአራዳ ቃላት ተጠቃሚዎች ማህበራዊ ክፍልና በነባራዊ ባህል መካከል ሚደበላለቅ መኖር ወጣቱ የህብረተሰቡ አንድ ክፍል እንደመሆኑ ላለው ባህል ተገዥ እንዲሆን ይገመታል፡፡ እንደምናየው ግን ተገዥነቱ ባህሉን በሙሉ ወይም በደግ አይኑ እንዲመለከት አላገደውም፡ ባህሉን ተቀብሎ ታማኝነቱንም ያረጋገጠም ሚይቷል፡፡ በሌላ በኩል ከባህሉ አፈንግጦ ወጥቷል፡፡ በሚደበኛው ቋንቋ ለውጥ ለሚደግ ሰፊው እድል የተዘረጋለት ለአራዳ ቃላት ነው፡፡ የዘመኑ አባባል ተጠቃሚዎች በቁጥር ብዛት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በየቦታው የተሰራውና እነዚህ በየቦታው ያሉ ተጠቃሚዎች ይህንን አባባል ከሚደባኛው ቋንቋ በሚደባለቅ ስለሚናገሩት የሚደበኛው ቋንቋና የአራዳ ቃላት ፍች ከፍተኛ ሆኖ ለለውጥ ላይበቃ ይችላል፡፡ ሌሎች መግባቢያዎች ግን የሚለገሉባቸው ቡድኖች ጥቂት ስለሆኑ በተወሰነ አካባቢ የተከለሉ

በመሆናቸውና መገባቢያቸው በይፋ ሲያገለግል የስራ ፀባያቸው ስለሚፈቅዳላቸው ከሚበኛው ቋንቋ ያላቸው ፍጭት አነስተኛ ነው በመሆኑም በሚበኛው ቋንቋ ላይ የሚያደርጉት ለውጥ የሚያሳስብ አይነት አይሆንም፡ የአራዳ ቃላት የተወሰኑ አይደሉም፡ የአባባሉ አካል ለመሆናቸው የሚዋቀርላቸው በቃላቱ ላይ አንዳችም አይነት ማሻሻያ አልተደረገባቸውም ቃላቱም ሆኑ አባባሎቹ የአራዳ ቃላት ላለመሆናቸው የሚዋቀርላቸው የሚጠቀሙባቸው ግለሰቦች፣ ቃላቱ እና አባባሎቹ የሚያስተላልፉት መልዕክት ነው፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ያላቸው የወፍ ቋንቋ፣ የጓዳ ቋንቋ የዘየ ተጠቃሚዎች፣ የአራዳ ቃላት ተጠቃሚዎች ስለሆኑ በዚህ ክልል የሚካሄቡባቸውን ቃላቱና አባባሎች የአራዳ ቃላት ክፍል ሊያደርጓቸው ይችላሉ ዘለቀ (1977)፡፡

## 2.6 የውሰት /Borrowing/ ምንነት

*የቋንቋ ውሰትን* /borrowing/ *ምንነትን በተመለከተ አንድ ወጥ ብያኔ ባይኖርም በርካታ የሥነ ልሳን ምሁራን እንደጥናታቸው ዓላማና ግብ የተለያዩ ፍችዎችን ሰጥተዋል፡፡ የሻው*(1996)፣ Winford (2003) *ጠቅሶ እንደገለፀው ውሰት"ለአንድ ንግግር ሲባል የምንጠቀምበት ቃል ሆኖ ህግ የማናበጅለት ነው" ሲል ይገልፃል፡፡ስለሆነም ውሰት አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር በተለያዩ አውዶች እና በማህበረዊ መስተጋብር ምክንያት የቃላት ውሰት ይካሄዳል፡፡ከዚህ በተጨማሪም የ*Winford*ን ሀሳብ የሻው* (1996) *በቋንቋዎች መካከል የቋንቋ አካላትንም* (*ቃላት፣ ሐረጋት፣ የእርባታ ምዕላዶች*) *እና የአገላለጽና የመዋቅር መልኮችን መዋዋስ የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ወደፊትም የሚቀጥል ጉዳይ ነው፡፡መዋዋስን የገታ የአንድም ማህበረሰብ ታሪክ አልተመዘገበም፡፡አንዳንድ ቃላት ቁርጥ አማርኛ ይመስሉን እንጂ በተውሶ የተወሰዱ የተወሰዱ ናቸው፡፡ፊርማ፣ መኪናና ስኳር፣ ወና* (*ኦና*)፣ *ይፋ* (*ኢፋ*) *ኪሎ፣ ኮት፣ መዲና ይጠቀሳሉ፡፡ነገር ግን የአማርኛ ቅርጽን በማስያዝ ፊርማ "ፈረመ" ዳንስ "ደነሰ" ይፋ "በይፋ" እየተገለገልንባቸው ነው*(*የሻው*፣1996)፡፡ *የአንድ ቋንቋ ማህበረሰብ ፈጽሞ ብቻውን መኖር እንደማይችል እና ከማህበረሰቡ ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ተግባቦት ወይም የሀሳብ ልውውጥ ያደርጋል፡፡ከዚህ የተነሳ የቃላት፣ የሐረጋት፣ የቅጥያ ምዕላዶች፣የአገላለጾች እንዲሁም አንዳንዴ መረን ለቀቅ የቋንቋ ውሰት ከባህል ጋር በተያያዘ ሊፈፀም ይችላል* (Bloomfield ፣1961)፡፡

*በሌላ በኩል* (Bloomfield፣1961) *እንደሚለው የቋንቋ ውሰት ሥነ-ልሣናዊ ብቻ ሳይሆን ባህላዊ ተላልፎውንም ይጨምራል፡፡ የቋንቋውን ውሰት የሚያስከትሉ ጉዳዮች ከባህል*

*ጋርም ይያያዛሉ ማለት ነው፡፡ ቃላትንም ሆነ የአገላለፅ መንገዶችን የሚዋስ ማህበረሰብ የሚዋስበትን ቋንቋ የሚገነዘበው ከራሱ ላቅ አድርጎ ነው፡፡ለምሳሌ እኛ ከእንግሊዝኛ ቃላትን በብዛት የምንዋስ ከሆነ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችን ከእኛ የላቁ ህዝቦች እንደሆኑ እናስባለን ማለት ነው፡፡በዚህ የተነሳ ተገቢ ከሆነ ሰብዓዊና ምርታዊ ግንኙነትን አልፈን፣ የአለባበስ፣ የአኗኗር፣ የጋብቻ፣ የባህሪይ ወዘተ…ቅጅዎችን ሁሉ ከቋንቋው ጋር ማምጣት እንመኛለን፡፡ይህ ደግሞ የራስን ማንነት ዝቅ ማድረግ ነው፡፡*

በአጠቃላይ ቃላት ሀሳብን ለመግለጽ አይነተኛ መሳሪያ ናቸው፤ ሁሉም ቃላት ግን እኩል ሀሳብን የመግለጽ ብቃት አይኖራቸውም፤ ተገቢና ተስማሚ ቃላት ለተግባቦት መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ተግባቦትን የሚያቀላጥፍ የቃላት አጠቃቀሞች መካከል እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አውዳዊ ቃላት አማካያ (ማክሼ) ቃላት ደምጸ–ቀድ ቃላት ፈሊጣዊ ቃላት ተጠቃሽ ናቸው፡ እንዲሁም ተግባቦትን የሚያውኩ የቃላት አጠቃቀሞች መካከል ተገቢ ያልሆነ የቃላት ድግግሞሽ የቃላት ድረታ የባእድ ቋንቋ ቃላትና ሀረጋት የተሰለቹ ቃላትና አገላለጾች /ክልሼ ቃላት /ሀራም ቃላት /Taboo/ ዘዬ ቃላት እና የአራዳ ቃላት ተጠቃሾች ናቸው፡

የአራዳ ቃላት ማለት በአንድ በተወሰኑ ማህበራዊ ክፍል በተለይ በወጣቶች ለአንድ ግልጋሎት ሲባል የሚፈጠሩ ቃላት ናቸው፡ ቃላቱ አዲስ ፈጠራ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ምንጫቸው መደበኛ ቋንቋው ነው፡ ሆኖም በተለየ ዓላማ ስለሚለገሱበት በቅርጽ ላይ ለውጥ ይፈጥሩበታል፡፡ አለበለዚያም ተጨማሪ ትርጉም ይሰጡታል ግልጋሎታቸውም ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ነው፡ የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ በሙሉ ሊያግባባ አይችልም፤ ወጥነት አይታይባቸውም ወጥነት ይጎድላቸዋል፤ ከቦታ ቦታ ይለያያሉ ሰሞነኛ (ጊዜያዊ) ናቸው

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.1 የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

ይህ ጥናት በአይነታዊ የምርምር ዘዴና ገላጭ ተንታኝ የአተናተን ስልትን በመከተል በማገር እና በመጻፍ ጊዜ የአራዳ ቃላት የአጠቃቀም ስርጭቱን በማሳየት የቃላቱን አፈጣጠር ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም የአራዳ ቃላት የአጠቃቀሙ ስርጭት ከተመለከተ በኋላ መረጃውን ሰብስቦ፣ ተንትኖ መደምደሚያ አስቀምጧል፡፡ ከዚህ አንጻር አጥኚው በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በአንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀማቸውን በአካል ተገኝቶ በመመልከት ፍተሻውን አድርጓል፡፡

### 3.2 የሚጃ ናሙና አወሳሰድ ስልት

አጥኚው ጥናቱን በሚያካሂደበት ጊዜ የተጠኚወዳና የአካባቢወዳ ናሙና ማሚጥ አስፈላጊ በሚሆኑ ጥናቱን የሚያካሂደበትን ቦታ በቀላል የእጣ ናሙና መሰረት የተሚጠ ሲሆን ሂደቱም አስሩንም ክፍለ ከተማ ስም ዝርዝር በእጣ መልክ በማዘጋጀት እጣው የወጣለትን ቂርቆስ ክፍለ ከተማን የጥናቱ ቦታ አድርጎ ሲወስድ በክፍለ ከተማው የሚገኙትን አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤትን በአጠቃላይ የጥናቱ አካል አድርጎ ወስዷል፡፡ከዚህም አንጻር አጥኚው የጥናት ናሙናወዳ የወሰደው በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ከተሚጡቱ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት ሚጃወዳ ሰብስቧል፡፡በአጠቃላይ ከአራት ሺ አምስት መቶ ዘጠና ሶስት (4593)ተማሪዎች ውስጥ አስር(10) ፐርሰንቱን የግኝት ናሙና ዘዴን በመጠቀም የጥናቱን ተሳታፊዎች የሆኑትን አራት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ(459) ተማሪዎችን አሳትፏል፡፡

#### 3.2.1 የጥናቱ ቦታ

አጥኚው ለዚህ ጥናት የሚጠው ቦታ በአዲስ አበባ የሚገኙትን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶችን ነው፡ በአዲስ አበባ አስር ክፍለ ከተሞች አሉ፡ ከነዚህ ክፍለ ከተሞች ውስጥ በቀላል የእጣ ናሙና አወሳሰድ ስልት መሰረት ቂርቆስ ክፍለ ከተማን የጥናቱ ቦታ አድርጎ ወስዷል፡፡ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ የሚገኙ አራት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት በጠቅላይ ናሙና ተወስዷል፡፡

#### 3.2.2 የጥናቱ አካላይ

አጥኚው የተማሪዎች የአረዳ ቃላት አጠቃቀም ለሚቲተሽ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት የጥናቱ አካላይ አድርጎ ወስዷል፡፡እነሱም ሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ምስራቅ ጎህ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣የተባበሩት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ጠማጃ ያዥ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና አብዮት ቅርስ መሰናዶ ትምህርት ቤት ናቸው፡በነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 1958 ወንድ ተማሪዎች እና 2635 ሴት ተማሪዎች ይገኛሉ፡ በአጠቃላይ በደምሩ 4593 ተማሪዎች ይገኛሉ፡ከዚህ አጠቃላይ የተማሪ ብዛት ውስጥ 10 ፐርሰንቱን 459 አራት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ተሚጧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፡ የጥናቱ አካላይ ዝርዝር**

| ተቁ | የት/ቤቱ ስም | የተማሪ ብዛት | | ደምሮ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ወ | ሴ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 563 | 848 | 1411 |
| **2** | ምሥራቅ ጎህ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ወ | ሴ | |
| | | 365 | 451 | 816 |
| **3** | የተባበሩት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ወ | ሴ | |
| | | 92 | 69 | 161 |
| **4** | ጦሟጃ ያዥ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | ወ | ሴ | |
| | | 434 | 594 | 1028 |
| **5** | አብዮት ቅርስ መካናዶ ት/ቤት | ወ | ሴ | |
| | | 504 | 673 | 1177 |
| | ድምር | | | 4593 |

### 3.2.3 የናሙና ብዛት መወሰን

በዚህ ጥናት ውስጥ እያንዳንዱን ተማሪ በመረጃ ምንጭነት መጠቀም አስፈላጊ ባለመሆኑ የናሙና መጠን መወሰን ተገቢ ሆኖ አጥኚው ስላገኘው በ Dawson (2006) ከ 5-20 % የናሙና መጠን አስተማማኝ ነው በማለት በገለፀው መሰረት አጥኚው 10%ቱን ወስዷል፡፡ ምክንያቱም በርካታ የአካላይ ቁጥር ላላቸው 10% መውሰድን ሲመክር የአካላይ ቁጥራቸው ትንሽ ለሆኑት 20% ናሙና መውሰድ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት የናሙና ብዛት 459 ይሆናል፡፡የጥናቱ አካላይ በርካታ ቁጥር ስለያዘ አጥኚው ይህንን መሰረት በማድረግ ከያንዳንዱ የጥናቱ አካላይ ትምህርት ቤት 10% ናሙና በመውሰድ ጥናቱን ሰርቷል፡፡ሰንጠረዥ 2 ይህንን በዝርዝር ያሳያል፡፡

**ሰንጠረዥ 2 የጥናቱ ናሙና በየትምህርት ቤቱ ዝርዝር**

| ተቁ | የት/ቤቱ ስም | የተማሪ ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 141.1 |
| 2 | ምሥራቅ ጎህ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 81.6 |
| 3 | የተባበሩት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 16.1 |
| 4 | ጦሟጃ ያዥ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 102.8 |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | አብዮት ቅርስ መስናዶ ት/ቤት | 117.8 |
| | ድምር | 459.4 |

### 3.2.4 አመቺ ወይም ግኝት ናሙና ዘዴ

አመቺ ወይም ግኝት ናሙና ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ምክንያቱም የአራዳ ቃላት ቡድናዊ በመሆኑ አጥኚው በየትምህርት ቤቶቹ መረጃን ለማሰባሰብ በተንቀሳቀሰበት ቦታ ሁሉ ትኩረቱ በቡድን በቡድን ሆነው ጊዜያቸውን አብረው የሚያሳልፉ ተማሪዎችን በመውሰድ ቡድናዊ የቃላት አጠቃቀም መኖሩን መመርመር የአጥኚው ተቀዳሚ አላማ በመሆኑ ይህንን ግኝት ወይም አመቺ የናሙና ዘዴን ተጠቅሟል፡፡

አጥኚው ጥናቱን በቅርበት ባገኛቸውና ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ የሆኑለትን ተማሪዎች በመምረጥ ጥናቱን አጥንቷል፡፡ ይህም የተባለበት ዋና ምክንያት አጥኚው ጥናቱን ሲያካሂድ በቅርበት የሚያገኛቸውን ተጠኚዎች በታና ጊዜ ያገጣጠሟቸው በመሆኑ ነው፡

ከዚህም አንፃር ይህ የናሙና ዘዴ በጣም የተለመደና አብዛኛውን ጊዜ አንድን የጥናት ርዕሰ ጉዳይ መሰረት አድርጎ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ሲባል የሚደረግ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው፡ ይህ የናሙና አመራረጥ የሚያካትተው የተመረጡ ናሙናዎችን በመጠቀም ጠቅለል ያለ መረጃ የማሰባሰብ ስራ የሚሰራበት ነው፡ ስለሆነም ዓላማን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ አካባቢዎችንና ተጠኚዎችን በናሙናነት ወስዷል፡፡

### 3.3 የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

ጥናቱን በተገቢው መንገድ ከግብ ለማድረስ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመምረጥ አስፈላጊውን የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅፆችን አዘጋጅቶ እና የጊዜ ሰሌዳን መድቦ የጥናቱን ዓላማ በተገቢው መንገድ ለማከናወን የሚረዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ እነሱም –

### 3.3.1 ምልከታ

አጥኚው ጥናቱን በሚያከናውንበት ሂደት በተማሪዎቹ የንግግር ውስጥ የሚጠቀሙትን የአራዳ ቃላት ለማጥናት የንግግር ሂደታቸውን መደበኛ በሆነ መልኩ በመመልከትና በመመዝገብ ለጥናቱ ግብአት ማሰባሰቢያ እንዲሆነው ተጠቅሞበታል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚኖራቸው ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ የሚያደርጉትን ተግባቦት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በመዘዋወር የሚናገሯቸውን የአራዳ ቃላት በመመዝገብ ነው፡ ይህም የምልከታ ሂደት የተከናወነው በተማሪዎቹ የእረፍት፣ የምሳ ሰአት፣ የእግር ኳስ፣ የመረብ ኳስ እና ቅርጫት ኳስ ሲጫወቱ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በመዘዋወር በቡድን በቡድን እየሆኑ የሚጫወቱ ተማሪዎችን ንግግር ግንዛቤው ኖሯቸውም ሆነ ሳይኖራቸው መደበኛ ተግባቦታቸውን

በማዳመጥና በመመልከት መረጃውን ሰብስቧል፡፡ ከላይ ለቀረቡት የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ሲል በትኩረት መረጃውን ለማሰባሰብ የሚጠቀምበት ስልት ስለሆነ በሂደቱ ውስጥ በቂ ጊዜ ወስዶ ተማሪዎቹ የሚጋገሩባቸውን ቃላት በመመልከትና በመመዝገብ ለጥናቱ ደጋፊ መረጃን መሰብሰብ ተችሏል፡፡በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና አንድ መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች የንግግር ሂደትን በመመልከት የሚጠቀሙትን የአራዳ ቃላት እየመዘገበና ትርጉማቸውንም እየጠየቀ የቃላቱን አፈጣጠር ለይቶ በዝርዝር ለማቅረብ ተችሏል፡፡ይህም ሲባል አጥኚው ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ ከቢጤዎቻቸው ጋር በሚሆኑበት ወቅት የሚገሩትን ቋንቋ ለመመርመር ምልከታን እንደ መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡

#### 3.3.1.1. በአቻ ተማሪዎች መረጃ መሰብሰብ

በተጨማሪም ለጥናቱ በተመረጡ አምስት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ከየትምህርት ቤቶቹ አንድ አንድ በደምሩ አምስት መምህራንን በታላሚ የናሙና ዘዴ በመምረጥ መምህራኑ መረጃውን በታማኝነት ይሰበስባሉ ያሏቸውን ተማሪዎች በታላሚ ናሙና ዘዴ ከየትምህርት ቤቶቹ ሶስት ሶስት በጠቅላላው 15 (አስራ አምስት) ተማሪዎችን በመምረጥ እና ስልጠና በመስጠት ተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀማቸውና ትርጉማቸውን በቢጤዎቻቸው ማሰብሰብ ሁለተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል፡፡

### 3.3.2 ድርሰት ማፍ

የአማርኛ ትምህርት ዋና አላማ የተማሪዎቹን የመናገር፣የማዳመጥ፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች እንዲያበለጽጉ ማድረግ ነው፡አጥኚው የአራዳ ቃላትን ለማጥናት የመረጣቸው የመናገርና የመጻፍ ክሂሎችን ሲሆን በነዚህ ክሂሎች ውስጥ ተማሪዎቹ በሚጽፉበትና በሚገሩበት ጊዜ የቃላት አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፡በዚህም መሰረት ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የቃላት አጠቃቀም መመርመሮን ሦስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡በመሆኑም ተማሪዎቹ በ9(ዘጠኝ) የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ድርሰቶች እንዲያጽፏቸው የአማርኛ የቋንቋ መምህራንን በመጠየቅ ተማሪዎቹን ድርሰት አጽፈዋቸዋል፡፡እያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ በአስር በአስር ተማሪዎች እንዲፃፍ ተደርጓል፡፡የተማሪዎቹ አመራረጥ ከውጤት መመዝገቢያ ላይ የተማሪዎቹን ቁጥር በመውሰድ የመማሪያ ክፍሎቹን በቀላል የእጣ ናሙና በመምረጥ ሲሆን እነዚህን ተማሪዎች የሚያስተምሩ ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ በደምሩ አምስት መምህራንን በታላሚ ናሙና መሰረት ሊመረጡ ችለዋል፡፡የማየት ሂደቱም መምህራኑ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአራዳ ቃላትን እንዲለዩ በማድረግ ነው፡የማየት ሂደቱም ተማሪዎቹ የፃፏቸውን ድርሰቶች ኮፒ በማድረግ እንዲለዩ ከተደረገ በኋላ በሶስቱ ተመሳሳይ የሆኑትን በማየት ለማንተን ተችሏል፡፡እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የተፃፉት በ50(ሃምሳ) ተማሪዎች ነው፡ በዚህም መሰረት ለትንተና የተመረጡየድርሰት ርዕሰ ጉዳዮቹ ፡-

(1) ጀሎ ማክቤል የተሰኘው ድርሰት ሰደከት ገጾች ሲኖሩት በአስራ ሰባት በስምት አንቀጾች

ተገንብቷል፣

(2) ሰውና ስያሜው በሚል የተፀፈው ድርሰት ደግሞ ሣሥት ገፅ ሲኖረው በስምንት አንቀፆች ተገንብቷል፡፡

(3) በሰዓት ጨዋታ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት ደግሞ ሶስት ገጽ እና ዘጠኝ አንቀጾች አሉት፣

(4) የማታ እንጀራ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት ሶስት ገጾችና ስድስት አንቀጾችን ይዟል፣

(5) ግራና ቀኝ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት ሶስት ገጽና አስራ አንድ አንቀጾችን የያዘ ድርሰት ነው፡፡

(6) ሳባ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት አራት ገጽ እና ስድስት አንቀጾች ይዟል፣

(7) ባለመጽሀፍ ቤቱ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት በአምስት ገጾችና በአምስት አንቀጾች ተገንብቷል፣

(8) ጨዋታ በሚል ርዕስ የተጻፈው ድርሰት ደግሞ አራት ገጾችን የያዘ ሲሆን የቀረበውም በምልልስ ነው የሚጨረሻው

(9) የተያያዙ ልቦች በሚል ርዕስ የተጻፈ ድርሰት ሲሆን በሁለት ገጽና በአራት አንቀጾች ተገንብቷል፡፡

እነዚህ በተሚዎች የተፃፉ ድርሰቶችን የቃላት አጠቃቀማቸው የአራዳ ቃላት በውስጣቸው በማዛቸው አጥኚው ቃላቶቹን እየመዘገበ በማጥናት የቃላቱን ትርጉምና አፈጣጠር በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

### 3.3.3 የጽሁፍ መጠይቅ

አጥኚው የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ዙሪያ ዝግ እና ክፍት መጠይቅ የጥናቱን ዝርዝር ዓላማ መሰረት በማድረግ አዘጋጅቷል፡፡የነዚህን ጥያቄዎች የሰዋስውና የፊደል ግድፈት ለሚያም ይረዳ ዘንድ ለቋንቋ መምህራን በማሳየት ጥያቄዎቹን አሻሽሏል፡፡ይህ የጽሁፍ መጠይቅ በውስጡ አራት መሰረታዊ ክፍሎች አሉት፡፡የመጀመሪያው የተሳታፊዎች ዳራ ሲሆን ይህም የተሚዎችን የትምህርት ደረጃ ፣ፆታ እና ትምህርት ቤት ለማሳየት አገልግሏል፡፡ሁለተኛው ክፍል የአራዳ ቃላትን በህሪያት መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ሶስተኛው ክፍል በማግባር ሂደት የአራዳ ቃላት አጠቃቀም የተግባቦት ክፍተት መኖሩን ማሳኪያ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን አራተኛው ክፍል የአራዳ ቃላት ለጥናቱ በተሚጡ ትምህርት ቤቶች የአገልግሎት ስርጭቱን መጠን ለማሳካት ተጠቅሞበታል፡፡

## 3.4 የሚጃ አተናተን ዘዴ

አጥኚው የሰበሰበውን ሚጃ ለትንተና ከማቅረቡ በፊት በትክክል መጠናቀራቸውንና ሚደራጀታቸውን አረጋግጧል፡፡ይህም ማለት የተሰበሰቡት ሚጃዎች ለትንተና በሚሄዱ ሚልኩ በማስተካከል በየተሰበሰቡበት በምልከታ እና በአቻ ተሚዎች የተሰበሰቡ ሚጃዎች አንድ ላይ፣ከድርሰት የተገኙትን ሚጃዎች አንድ ላይ

በማድረግ እና ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙትን ደግሞ አንድ ላይ አድርጎ ተንትኗል፡፡ ከዚያም በየፈርጁ የተቀመጡትን መረጃዎች በርዕስ በርዕሳቸው በማልቀም ተመሳሳይ ጭብጥ ያላቸውን አንድ ላይ በማድረግ አጥኚው አቀናጅቶ በማተንተን አቅርቧል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በተሰበሰበው የመረጃ አይነት የተሰበሰበውን መረጃ በሚገባ እና ለመረጃው ስያሜ በመስጠት ለትንተና ስራ በሚመች መልኩ ለማቅረብ ተችሏል ፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ለ459 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆችን የበተነ ሲሆን ከነዚህ መጠይቆች መካከል በትክክል ያልተሞሉ እና ያልተመለሱ 16 መጠይቆችን ከትንተናው ውጭ አድርጎ ቀሪዎቹን 443 መጠይቆች በመጠቀም ተንትኗል፡፡

አጥኚው በምልከታ፣ በአቻ ተማሪዎች፣ በድርሰት ጽሁፍ እና በጽሁፍ መጠይቅ የሰበሰበውን መረጃ በገላጭ ተንታኝ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም መረጃውን ተንትኗል፡፡ ይህ የመረጃ አተናተን ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በተማሪዎች ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም በመማር ማስተማር አውድ ውስጥ በማገር እና በማፃፍ ክሂል ላይ የሚፈጥረውን የተግባቦት ክፍተት በሚገባ ተንትኖ አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ከዝግ መጠይቅ የተገኙትን ምላሾችንም በገላጭ ተንታኝ የአተናተ ስልትን በመጠቀም ተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. የመረጃ ትንተና ውጤት

አጥኚው አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ተማሪዎች የአራዳ ቃላት አጠቃቀም ሚፈጥረው አላማ በማድረግ ይህንን ጥናት አካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት ያነሳቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጥባቸዋል፡፡ ለዚህም ምልከታ፣ የአቻ ተማሪዎች፣ የፅሁፍ መጠይቅ እና በተማሪዎች የተፃፉ ድርሰቶችን ተተንትነው በዚህ ክፍል ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 የተሳታፊዎች ጻታ ትንተና

**ሰንጠረዥ 3፡ የተሳታፊዎች ጻታ**

| ፆታ | የሚሎጭብዘት | ፐርሰንት |
|---|---|---|
| **ሴት** | 130 | 29.4 |
| **ወንድ** | 313 | 70.6 |
| **ደምር** | 443 | 100 |

በሰንጠረዥ 3 ላይ እንደሚሂየው በዚህ ጥናታ ላይ ከተሳተፉት መካከል 130(29.4%) ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 313 (70.6%) ወንዶች ናቸው፡ሚኟጃወዓ ለመሰብሰብ አጥኘው ግኝት ናሙ ስለተጠቀመ በቡድን ሆነው ለሚቀሳቀሱ ተሜሪዎች ትኩረት ሰጠ እንጂ ፆታን በተለየ ሜኤኩ በሞት የአራዳ ቃላትን ከፆታ አኳያ ለሞት ባለማቅሩ በዚህ ትንተና ላይ የወንዶች ቁጥር በዛ ብሎ ታይቷል፡፡ በዚህ ቅኝት ትኩረት የተደረገበት የትንታኔ አካሄድ የመላሾችን ደምሮ ሜኤስ የሚኟኮዝ እንጂ በፆታ፣በዕድሜ እና በሚኟጁበት ትምህር ቤት አመቅኘነት በሚኘ የተለያዩ ተባቅሮዎች ከሚሳደሯቸው ተጽእኖዎች አንጻር አለመሆኑን እንዲታወቅ አስቀደሞ ማጠቆም ይፈልጋል፡፡

### 4.1.2 ከምልከታ የተገኘው የወቶት ትንተና

በዚህ ምልከታ ሂደት አጥኚው በአምስት ትምህርት ቤቶች ወስጥ እየተዘዋወረ የተሜሪዎቹን ንግግር በማዳሙጥ የሰሙቸውዓ እና በአቻ ተሜሪዎች የተሰበሰቡ የአራዳ ቃላትን በመመዝገብ 494(አራትመቶ ዘጠና አራት) የአራዳ ቃላትን አፈጣጠር መቅረት በሚድረግ በዝርዝር ትንትኖ አቅርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡ አዳስ ወይም አመጣጣቸው ያልታወቀ ቃላትን በመፍጠር የተገኙ የአራዳ ቃላት**

| ተ.ቁ. | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም | ተ.ቁ. | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቃርማ/ቆምጥር/ባቢለን | ፖሊስ | 15 | ጀዋል | ተንቀሳቃሽ ስልክ |
| 2 | ሳቢ | ብር | 16 | ጢጥ | ሽማግሌ |
| 3 | ሴሎ/ቦዛ | ጠላ | 17 | ዉጅ | ማንኛውም ፖሊስ |
| 4 | ረሃ | ፈታ ማለት | 18 | ሳንቁራ | ምንም የማያውቅ |
| 5 | ኮላ | ስኳር | 19 | እንፋጥ | እንሂድ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ቄንበ | ምንም የማይፈራ | 20 | ጁት | ቁሚር |
| 7 | ቾግ | ሲጋራ | 21 | ፓፍ | ሲጋራ |
| 8 | አቼ/ቦግ/ንበ | ጡጅ | 22 | ቻፓ | ገንዘብ |
| 9 | ሞኑሌ | ማፈሻ | 23 | ፈዋ | ምግብ |
| 10 | ሞኑቂ | አንባሻ | 24 | ጨፀ | ወርቅ |
| 11 | ቆንቆ | ምግብ | 25 | ዋኞ | ውሃ |
| 12 | ጋላጌ | የኪስ ቦርሳ | 26 | ሞቹሪም | ሌባ |
| 13 | ዋዬ | ሞጣ | 27 | ላላንቴ | ኮፍያ |
| 14 | ጩልለች | አበደች | 28 | ኑንዲ | ንፉግ |

ከላይ በሰንጠረዥ 4 እንደሚታየው 28 (ሃያ ስምንት) ቃላት አጥኚው በምልከታ ሂደት በጥናቱ ስፍራ ያዳመጣቸው የአራዳ ቃላት ናቸው፡ እነ ዚህም ቃላት እንደሚያሳዩት በአምስቱም ትምህርት ቤቶች ተሚዎች እየተጠቀሙ ያሉ የአራዳ ቃላት ሲሆኑ ወቅታዊ ትርጉማቸውም ተመሳሳይ ነው፡ ከዚህም በተጨማሪ አፈጣጠራቸው ተናጋሪዎቹ የፈጠሯቸው ናቸው፡ ይህ የሚያመለክተው የአራዳ ቃላት አስቀድመው ተናጋሪዎቹ በስምምነት ላይ በተመሰረተ መንገድ ትርጓሜ በመስጠት እንደተፈጠሩ ያመለክታል፡፡ ይህ ጥናት አዲስ ቃላት መፍጠር የሚችሉ የአማርኛ ቃላት ያልሆኑትን እና አፈጣጠራቸው ለሚደበኛ ቋንቋ ተናጋሪው እንግዳ የሆኑትን ለማመልከት ነው፡ ለምሳሌ አቼ፣ ዙጥዬ፣ ጋላጌ፣ ቻፓ፣ ቾግ፣ ዋዬ፣ የሚሉትን ቃላት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንን ሚጃ (Pmario1994) ሲያጠናክረው የአራዳ ቃላት ተጠቃሚ ቡድኖች የሚፈጥሯቸው አዳዲስ ቃላት አፈጣጠራቸው የሥነ-ልሳንን መሰረታዊ ሀሳብ የሚከተል ማለትም እንደ ሚደበኛው ቋንቋ የሰዋሰው አወቃቀርን የሚከተል መሆኑንና ከቡድኑ አባላት ውጪ ለሆኑ ሊያግባባ እንደሚችልም በጥናቱ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር የአራዳ ቃላት በተግባቦት ሂደት ላይ ክፍተት እንደሚፈጥር ከሚጃው ለሚዳት ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፡ ተጨማሪ ትርጉም በመስጠት የተፈጠሩ የአራዳ ቃላት**

| **ቁ.** | **የአራዳ ቃላት** | **የአማርኛ ትርጉም** | **ቁ.** | **የአራዳ ቃላት** | **የአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማለኛ | ሀብታም | 27 | በሰለ | ተገኘ፣ በእጅ ተደረገ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ስደስት | ዝም በል/ይ | 28 | ሸጢረኝ | ደበቀኝ |
| 3 | አትርገጠኝ | ጡጭጬ ገራብ | 29 | ሰለሞኝ | ያገለገለ ልብስ |
| 4 | ሚጢ | አደንዛዥ እጽ | 30 | ምቅኬ | ውሽማ |
| 5 | ጋዜጣ | እንጀራ | 31 | ሽታዬ | የከተማ አውቶብስ |
| 6 | አጎዛ | ጠላ | 32 | ፈውስ | ምግብ |
| 7 | ቆስቁሰው | ሂድ | 33 | ብርቄ | ስጋ ወጥ |
| 8 | ቋንጣ | የተሰጣ ልብስ | 34 | ማጫቅ | ሀምሳ ብር |
| 9 | ተከሰተች | ሞጫች | 35 | ሰፋሁት | አኮረፍኩት |
| 10 | ቆንጆዎቹ | ፌደራል ፖሊስ | 36 | ላውዳቸር | የአበሻ አረቄ |
| 11 | ቡሬ | ሜልክ የሌላት | 37 | አደንጓሬ | የሚጂብር ሰው |
| 12 | አስቀየሰ | ማገድ ለወጠ | 38 | ቀበሮዋ | ሴት ጓደኛው |
| 13 | አቀጣጠለው | አፋጠነው | 39 | ሸዋዬ | ያልሰለጠነ |
| 14 | አየለ | ፋራ/ያልሰለጠነ | 40 | ሞከብ | የቆሻሻ ገንዳ |
| 15 | ልጥልጥ | ሞኛሞኝ | 41 | ተቀንጠስ | ሂድ |
| 16 | አፎጋገረ | ቀያየረ/ደባለቀ | 42 | ማዥግ | ሚጩቅጩቅ |
| 17 | እንፈወስ | እንብላ | 43 | ግጨው | ስጠው |
| 18 | ከየፈቸኝ | አሚቺን | 44 | ባነነ | ነቃ |
| 19 | ወፍራም | ሀብታም | 45 | ልከርበት | ልሟስ |
| 20 | ወሾቹ | ፖሊሶቹ | 46 | አጣቢ | ሸምዳጅ |
| 21 | ዝብዝብ | ወሬ ማብዛት | 47 | ክቱ | ተከተለኝ |
| 22 | ይነገርበታል | ደስ ይላል | 48 | ሟ | ገንዘብ |
| 23 | ዲጄ | የታክሲ ረዳት/ወያላ | 49 | አይነፋም | ደስ አይልም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 24 | ጀማ | ጓደኛ | 50 | ኢቲቪ | ወሻታም |
| 25 | ፈለጣ | ማጥየቅ/መቀበል | 51 | ፎጣ | ብኩራም |
| 26 | ፍታኝ | ተወኝ | 52 | ሙቃ | አንገት |

ከላይ በሰንጠረዥ 5 የቀረቡት 52(ሃምሳ ሁለት) የአራዳ ቃላት አጥኚው በምልከታና በአቻ ተሜዎች የተሰበሰቡት በአምስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገሩ ሲሆኑ እነዚህ ቃላት በመደበኛው የአማርኛ ቃላት ላይ ተጨሜሪ ትርጉም በመስጠት የተፈጠሩ የአራዳ ቃላተ ናቸው፡ለምሳሌ ወፍራም የሚለውን የአማርኛ ቃል ትርጉም ተክለሰውነቱ የሞላ /የገዘፈ ሰውነት ያለው/ ማለት ሲሆን ይህንን ቃል አራደኛው ሀብታም የሚል ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ብርቄ የሚለውን የአማርኛ ቃል ትርጉም ስስቴ የሚል የአማርኛ ትርጉም ሲኖረው ይህንን ቃል በአራደኛው ስጋ ውጥ የሚል ትርጉም እንዲኖረው አድርገው ሲጠቀሙበት ወሾቹ የሚለውን የአማርኛ ስም ደግሞ የወሾችን ተግባር ከወስጡ በማውጣት ፖሊሶች የሚል ትርጉም እንዲኖረው አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ዲጄ የሚለውን የደምጽ ማጫቃ ማሳሪያ ከታክሲ ረዳት የስራ ተግባር ጋር በማመሳሰል ለታክሲ ረዳት ማጠሪያ ይጠቀሙበታል፡፡ከዚህ ሚኒጃ ሚኒዳት የሚቻለው የቋንቋው መደበለ-ቃላት በሆኑት ላይ ተጨሜሪ ትርጉም በመስጠት ምስጢራቸውን ማስተላለፍ እንደሚችሉና የቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ በመደበኛው ቃላት ላይ የተጠቀሙትን ተጨሜሪ ትርጉም ስለማያውቁት በንግግር ሂደት የተግባበት ክፍተት እንደሚፈጠር ሚኒጃው ያመላክታል፡፡ይህንንም ሚኒጃ ደረጄ(1996)ያጠናከረዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 6፡ በምሳላ ትርጉም በመስጠት የተፈጠሩ የአራዳ ቃላት**

| ተ.ቁ | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም | ተ.ቁ | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማሞሾ | ሽጉጥ | 12 | ሚጃ | ጎበዝ ተሜሪ |
| 2 | ቀዳዳ | ወሻታም | 13 | ቀለሜ | ጎበዝ ተሜሪ |
| 3 | ቆረሰ | ሄደ | 14 | ፍሙ | ሲጋራ |
| 4 | ቢጫ | ጠጅ/ሀምሳ ብር | 15 | ጥሬ | ገገማ |
| 5 | ግርግዳ | ጠንካራ ሰው | 16 | ሲዲ | አንባሽ |
| 6 | አስጨሁለት | ደውልላት | 17 | አሜድ | መቶ ብር |
| 7 | ጆሮ | ሰላይ | 18 | ቁምላቸው | ትራፊክ ፖሊስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ሸለቀቀ | ሳይሰማ ሰረቀ | 19 | ኬሚትሪ | አረቄ |
| 9 | ሞጅራ | ፈረንጅ | 20 | ኮረት | ስጋ |
| 10 | ጋቢና | ፊት | 21 | አጠበኝ | ገንዘቤን በላኝ |
| 11 | ሲዲ | አንባሻ | 22 | ቸካይ | ጎበዝ ተማሪ |

ከላይ በሰንጠረዥ 6 እንደተገለጸው 22(ሃያ ሁለት) የአራዳ ቃላት በሚከታው ሂደት አጥኚው ከጥናቱ ስፍራ ያዳመጣቸው የአራዳ ቃላት ሲሆኑ የቃላቱ አፈጣጠር ደግሞ ከሚደበኛው የአማርኛ ቃላት ጋር በማመሳሰል የተፈጠሩ ናቸው፡ ይህ ቃላትን በምሳላ የመፍጠር ሂደትን እንደሚከተለው በምሳሌ ማሳየት ይቻላል፡፡ ፍሙ የሚለዉን የተቀጣጠለ እሳት የሚያሳየዉን የአማርኛ የቃል ትርጉምን ሲጋራ የሚል የአራደኛ ትርጉም እንዲኖረው አድርገው ሁለቱንም ባላቸው የመቀጣጠል ባህሪ በማመሳሰል ቃላቱን ፈጥረው ይጠቀሙበታል፡፡ ማሞኘ የሚለዉን የአማርኛ ቃል ትርጉም ተናጋሪው ለተወለዱ ትናንሽ ህፃናት በአካል፣በአእምሮ እና በባህሪ ያልዳበሩትን ለማመልከት ሲጠቀሙበት አራዶቹ ደግሞ ትንሽ የሚለዉን በመውሰድ ከጦር መሳሪያ በማነስ ላነሰው ሽጉጥ መጠሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ ሞጅራ የሚለዉን የአማርኛ ቃል በሚልክ ነጭ ለሆነ ሰው መጠሪያነት ይገለገሉበታል፡፡ ሲዲ የሚለዉን ደግሞ አንባሻ ለሚለው ባህላዊ የምግብ አይነት መጠሪያነት ይጠቀሙበታል፡፡

**ሰንጠረዥ 7፡ ከውጭና ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በውሰት የተፈጠሩ የአራዳ ቃላት**

| ተራ ቁጥር | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም | | የአራዳ ቃላት | የአማርኛ ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሎካል | ያልሰለጠነ | 11 | ሹብ | ሽማግሌ |
| 2 | መዉረክ | መቅረት | 12 | ጨሌ | ገንዘብ |
| 3 | ሆላ | ሞኝ | 13 | ማዙካ | እናት |
| 4 | በያ | ጓደኛ | 14 | አቱካት | ንገራት |
| 5 | ቴስታታ | ጭቅላት | 15 | ችክ | ሴት |
| 6 | ችኳንታ | አምሳት ብር | 16 | ማጃም | እናት |
| 7 | ኮሌክሽን | የተረፈ ምግብ | 17 | ደቀሰ | ተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ፈያ | አባት | 18 | ቬንቲ | ሃያ ብር |
| 9 | ቀጀላ | የተስተካከለ ቆንጆ | 19 | ጀለስ | ጓደኛ |
| 10 | ፒን | የአበሻ አረቄ | 20 | ኛታ | በላተኛ |

ከላይ በሰንጠረዥ 7 እንደሚያየው አጥኚው በምልከታ እና በአቻ ተሚዎች የሰበሰባቸውን 20(ሃያ) የአራዳ ቃላት ሲሆኑ የተፈጠሩትም ከውጭና ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በውሰት በመውሰድ ነው፡ ይህ ከውጭ እና ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች በውሰት የገቡት ቃላት የአወሳሰዳቸው ሂደት ቃላቱን የአሚኛ ትርጉማቸውን እንዲይዙ በማድረግ ሲሆን ለምሳሌ ማዘም የሚለውን እናት የሚል ትርጉም ይሰጡታል፡፡ ይህንን ለማጠናከር ያህል ቴስታታ የሚለውን የኢጣሊያንኛ ቃል የአማርኛ ትርጉምን ጭንቅላትን እንዲወክል ተደርጎ አገልግሎት ላይ ያውሉታል፡፡ኛታ የሚለውን የኦሮምኛ ቃል በላተኛ የሚል የአራዳ ቃል እንዲሆን ተደርጎ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡በአጠቃላይ ይህ የውሰት ሂደት የሚያሳየው የሰው ለሰው እና የማህበረሰብ ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ ተግባቦት ወይም የሃሳብ ልውውጥ ያደርጋሉ፡ከዚህም የተነሳ የቃላት እና የአገላለጽ ውሰት ይፈፀማል፡፡ ይህንን በቋንቋው ውስጥ በውሰት የገቡትን ቃላት ደግሞ አራዳው ወደ ሚፈልገው ትርጉም በመቀየር ይጠቀምበታል ለዚህም እንደማሳያ ጀለስ የሚለውን እንግሊዘኛ ትርጉም ምቀኛ ሆኖ ሳለ አራደኛው ደግሞ በተቃራኒው ጓደኛ የሚል ትርጉም እንዲኖረው አድርጎ እንደሚጠቀምበት ያሳያል፡፡ ከዚህ ሚኖኝ ሚዳት የሚቻለው ውሰት የማንኛውም ቋንቋ ባህሪ መሆኑን ቢሆንም አራደኛው የሚዋሳቸውን ቃላት የበድሉ አባላት የፈለጉትን ትርጉም እንደሚሰጡ ጀለስ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉምን በተቃራኒው እንደሰጡቱ ለሚዳት ተችሏል፡፡ ውሰትን በተመለከተ Leslaw1964፣8)ሚበኛ ትርጉማቸውን እንዳለ ይውስዱና አራዶቹ የሚደበኛ ትርጉማቸውን በመቀየር እንደሚጠቀሙባቸው ይገልፃል፡፡

ሰንጠረዥ 8፡ ቃላቱ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በማለባበጥ የተፈጠሩ የአራዳ ቃላት

| **ተ.ቁ.** | **የአራዳ ቃላት** | **የአማርኛ ትርጉም** |
|---|---|---|
| **1** | ልባብ | ልብስ |
| **2** | ትሮጊ | አሮጊት |
| **3** | እንላብ | እንብላ |
| **4** | እንሙቅ | እንቃም |
| **5** | ይቻሙዋል | ይመቻቸዋል |

ከላይ በሰንጠረዥ 8 እንደተመለከተው አጥኚው 5 (አምስት) የአራዳ ቃላትን በምልከታው ወቅት የሰበሰባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ የሚያሳዩት በቃሉ ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቅደም ተከተላቸውን በማዘበራረቅ እንደተፈጠሩ ያሳያል፡፡ ይህ የሚያሳየው ልብስ የሚለውን የአማርኛ ቃል በመውሰድ የሆሄያቱን ስብጥር በማቀያየርና ሌላ ሆሄ በመጨመር የተፈጠረ ነው ለማሳየት ያህል "ል" እና "ብ" በመውሰድ በመሃላቸው "በ" በመጨመር ልበብ የሚል የአራዳ ቃል ፈጥረዋል ፡፡ በተጨማሪም አሮጊት የሚለውን የአማርኛ ቃል የሆሄያቱን ቅደም ተከተል ከቀኝ ወደ ግራ ሆሄያቱን በመውሰድ "ትን "በማስቀደም "ሮ" ና "ጊ" ቦታ በማቀያርና ''አ'' በማስቀረት''ትሮጊ'' የተፈጠረ ነው፡ በተጨማሪም የሚለውን የአማርኛ ቃልን "እን" የሚለውን ሆሄያቶች እንዳለ በመውሰድ "ብ" ና "ላ" ቦታ በማቀያየር ''እንላብ'' አራደኛው ተፈጥሯል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለቃሉ ተቃራኒ ትርጉም በመስጠት የተፈጠረ የአራዳ ቃል ራስታ የሚለው ሲሆን ትርጉሙም መላጣ የሚል ነው፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የአማርኛ ቃሉን የመጀመሪያ ሁለትና ሶስት ፊደላት በመጠቀም ከተፈጠሩት የአራዳ ቃላት መካከል ትሩ (ትርፍራፊ ምግብ) ፣መኩ (መኪና)፣ምዳሼ (ምድጃው)ና የሚጨ (የሚጨፈሸ) የሚሉትን ቃላት መዘርዘር ይቻላል፡፡ በሚጨፈሸም የቃሉን ፊደል ከግራ ወደ ቀኝ በማገልበጥ የተፈጠሩት የአራዳ ቃላት ለምሳሌ ጡሞ (ሞጡ)፣ፋጥ (ጥፋ) ፣ ትቤ (ቤት)፣ራቢ (ቢራ)፣ጋስ (ስጋ) እና ውሰ (ሰው) የሚሉትን ቃላት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ አጥኚው በምልከታ ሂደት የሰበሰባቸውን 494 (አራትመቶ ዘጠና አራት) የአራዳ ቃላትን የሰበሰበ ሲሆን የቃላቱ አፈጣጠር ከዚህ እንደሚከተለው ተንትኖ ያሳያል፡፡

- አዲስ ቃል በመፍጠር ለምሳሌ ቻፓ፣ ቸግ፣ ጋፍ፣ ፍሙጨሌ፣ ሙላ፣ ሻነው ወዘተ ናቸው፡
- ቃሉን ከቀኝ ወደ ግራ በማገልበጥ ለምሳሌ ትቤ፣ ጡሞ፣ ራቢ፣ ጡቂ፣ ፋጥ፣ ደሄ፣ ተሩ፣ ሞኪኬ እና ትሴ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡
- ለመደበኛው የአማርኛ ቃል ተጨማሪ ትርጉም በመስጠትለምሳሌ ሸዋዬ፣ ብርቄ፣ አየለ፣ ሾላ እና ስንቄ የሚሉትን ቃላት እንደ ምሳሌ ማየት ይቻላል ፡፡
- የአማርኛ ቃላትን የፊደል ቅደምተከትል በማዘበራረቅ ለምሳሌ ይቻማል ፣ ትሮጊ ፣ እንማቅ ፣እንፈጥ፣ ና ልባብን መጥቀስ ይቻላል፡፡
- የመደበኛውን የአማርኛ ቃል የመጀመሪያ ሁለት ወይም ሶስት ፊደላትን በመጠቀም ከሚፈጠሩት መካከል ለምሳሌ የሚጨ፣ምዳሼ፣ መኩ፣ ሞኪኬ እና ትምሮ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡
- ከሌላ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቋንቋዎች በመዋስ ለምሳሌ ደቀሰ፣ ቴስታታ፣ ጀለስ፣ በያ፣ ኮሌክሽን፣ ሙዚካ፣ ሙጃም እና ፒስ የሚሉትን እንደ አብነት ማሳየትይቻላል፡፡ ይህንን የምልከታ ትንተና ውጤት መሰረት በማድረግ አጥኚው በተማሪዎች የተፃፉ ድርሰቶችን በማንበብ ያገኛቸውን ቃላት ይዞታ ከዚህ በታች ባለው መልኩ ተንትኖ አስቀምጦታል ፡፡

### 4.1.3 ከተሜዎች ድርሰት ውስጥ የተገኙ የአራዳ ቃላት ትንተና ውጤት

"...በስካር ማፈስ ጥንቃቄ ሳናደርግ ለእርግዝና ተዳረግሁ፡፡በእዚያ ሰአት ለራሴ ክው ብልም ስነግረው ደስ ይለዋል አብረንም ስለምኖር እሱ የልጥጥ ልጅ ነው፡እኔም ደግሞ ትምህርት ስላቆምኩ ያገኘሁትን ዉርክ እዉርካለሁ ብዬ ስላሰብኩ ለእሱ ነገርኩት ግን ሁኔታው እንደጠበቅሁት አልነበረም፡ገና ስነግረው አንቺ ሸዋዬ መቅልከሽ እንዴ ቶሎ ብለሽ አስዉጪው ብሎ እጁ ላይ የነበረዉን ጨለ ገፍትሮልኝ ሚሽ፡፡...''ይህ ''ሳባ'' ከሚለው ድርሰት የተቀነጨበ ነው፡በዚህ መሰረት ከዚህ በመቀጠል በቅደም ተከተል ተተንትነዋል፡፡

ጀሉ ማክቤል በሚለው ድርሰት ውስጥ አረረረ...ችኳ፣ አቤት ጋቢና ከኔ ጋ ዱቅ በይ፣ሜ ነሽ፣የቅባት ልጅ ሳትሆን አትቀርም፣ቀዩን ተጫዉ፣ምን ታርፋለች፣ሊያዝገን ነው ፣ፎንቃ ፣ ጓደኞቿም ከች ብለው፣ለጩጪ ቻፓ እና ቬንቲ ዉረድ የሚሉትን መመልከት ይቻላል፡፡ቃላቶቹ የተፈጠሩት ጋቢና የሚለው ከመኪና የፊት መቀመጫ ተውስዶ የሰዉን የፊት ገጽታን የሚያመለክት ትርጉም ሲሰጠው ሜ ነሽ የሚለው ደግሞ ከመጽሀፍ አሳታሚ ሻጭ ተወስዶ ጎበዝ ተሜን የመግለጽ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡

ቀጥሎ ደግሞ የምናየው ጨዉዉት ከሚለው ድርሰት የተገኙትን የአራዳ ቃላት ይሆናል ፡፡ እነሱም ጀለሶች፣ ትምሮ፣ ቀላል አያካብዱ፣ጠንም፣ሸዋዬ ትሆንብኛለች፣ ሜድ የገባሽ የሚሉትን የአራዳ ቃላትን በድርሰቱ ውስጥ ለማካበብ ተችሏል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ላይ የሚታየው በሰዓት ጨዋታ በሚል ርዕስ የቀረበዉን ሲሆን በጽሁፉ ውስጥ ኩራዙ ህፃን፣ሸዉደና ሚሽ፣ ፍም አጫሹ፣የትሴ ነዉ፣ የትቤው ባለቤት፣ከፍም አራራ፣ረሃብ እየከሸከሻቸው እና ኩርባ ሜታ የሚሉትን የአራዳ ቃላት በድርሰቱ ውስጥ አገልግሎት ላይ ዉለው ተንኝተዋል፡፡ ኩራዙ፣ፍም እና ኩርባ የሚሉት የአማርኛ ቃሉ ተጨማሪ ትርጉም እንዲኖረው ተደርገው የተፈጠሩ ሲሆኑ ትርጉማቸው አጫፌ፣ ሲጋራ እና አታሎ ሄደ የሚሉ ትርጉም ሲኖራቸው ቀሪዎቹ ትቤ የሚለው ቤት፣ትሴ የሚለው ሴት ትርጉም ሲኖራቸው ቃላቱ የተፈጠሩት ሚደበኛዉን የአማርኛ ቃል ከቀኝ ወደ ግራ በማካበብ ነው፡

ቀጥሎ በአራተኛ ደረጃ ሳባና ባለመፅሃፍ ቤቱ የሚሉትን ድርሰቶች የያዙትን የአራዳ ቃላት የሚከተሉት ናቸው እነሱም አላስባንንም፣ላሽ በሉ፣ ዉርክ እዉርካለሁ፣በርጫዉን ፈጀሁት፣ምላ ዘጭ ብዬ የሚሉ ቃላት በድርሰቱ ውስጥ የተገኙ ዉርክ እዉርካለሁ የሚለው ቃል ከእንግሊዘኛ የተዉሰደ እና ስራ እሰራለሁ የሚል ትርጉም ያሳያል ፡፡

በመጨረሻም ሰዉና ስያሜው፣የሜታ እንጀራ፣የተያያዙ ልቦች እና ግራና ቀኝ ድርሰቶች ውስጥ የተገኙት የአራዳ ቃላት የሚከተሉት ናቸው፡እነሱም የመትነፋ፣በሳምንት ዱንጋ ጊዜ ያስቸክላል ፣ ካላንደር አርፋለች፣ ሜዙካዋ፣ ደንፎ ጫፈችብኝ፣ ፈታችሁን ጣልችሁት፣ ፈላ የነበረው ልጅ ዴቻ ክፍል፣አስደግፋ ቀረች፣ ማገዶ ቆጣቢ፣ ቀራኒዮ፣ ላሜራ፣ ንቦች ማደር፣ሽንኩርት ልጅ፣ ኤቨረዲ ፣ዉርቸባ ፣ጠጪ፣ወሜካ፣ ሾዳ፣

